# ትራኮማን እንዴት እንከላከል?



## ለመጀመሪያ ደረጃ አንደኛ ሣይክል የተዘጋጀ የመምህራን መምሪያ

**Curriculum For Trachoma Prevention**
**For Primary School Health Program**

## በካርተር ሴንተር ኢትዮጵያ የተዘጋጀ የአማርኛ ትርጉም


<u>በእንግሊዝኛ ያዘጋጁት</u>

ጄኒፈር ሉክስ **/Jennifer Loucks/**

ምሥራቅ መኮንን **/Misrak Makonnen/**



ሚያዚያ 1996 ዓ.ም



©1996 The Carter Center.

# ትራኮማን እንዴት እንከላከል ?

## ለመጀመሪያ ደረጃ አንደኛ ሣይክል የተዘጋጀ
## የመምህራን መምሪያ

# Curriculum For Trachoma Prevention For Primary School Health Program

## በካርተር ሴንተር ኢትዮጵያ የተዘጋጀ
## የአማርኛ ትርጉም


በእንግሊዝኛ ያዘጋጁት

ጄኒፈር ሉክስ /Jennifer Loucks/

ምሥራቅ መኮንን /Misrak Makonnen/

# ማውጫ


| | ገጽ |
|---|---|
| 1. መግቢያ | 1 |
| 2. ክፍለ ትምህርት አንድ | 13 |
| - የማየታችን አስፈላጊነት | 13 |
| 3. ክፍለ ትምህርት ሁለት | 23 |
| - የትራኮማ በሽታ ምንድን ነው? | 23 |
| - እንዴት ይተላለፋል? | 23 |
| - ዓይነ ስውርነትን እንዴት መከላከል ይቻላል? | 23 |
| 4. ክፍለ ትምህርት ሦስት | 35 |
| - የትራኮማ በሽታ መተላለፊያና መከላከያ መንገዶች | 35 |
| 5. ክፍለ ትምህርት አራት | 46 |
| - የትራኮማ ቀንን ስለማቀድ | 46 |
| 6. ተቀፅላ/ መገምገሚያ | 47 |

# መግቢያ

የትራኮማ በሽታ ክላሚዲያ ትራኮሚቲስ ከተባለ ህዋስ (bacteria) የሚመጣ ሲሆን ተገቢው ህክምና ካልተደረገለት ወደ ዓይነ ሥውርነት ሊያመራ ይችላል። በሽታው ቀስ በቀስ ዓይንን በመቆርቆር ስሜት እንባን በማንባት፣ በማቅላትና የፀሐይ ብርሃን በመፍራት ይታወቃል:: በመጨረሻ ደረጃ ላይ የደረሰ ትራኮማ ደግሞ የዓይን ቆብ ሽፋሽፍት ወደ ውስጥ እንዲቀለበስ በማድረግ ከፍተኛ የሆነ የመቆርቆር ስሜትና ስቃይን ያስከትላል። የዓይን ቆብ ሽፋሽፍት ወደ ውስጥ ሲቀለበስ የሽፋሽፍት ፀጉሩ የዓይን መስታወቱን (Cornea) አዘውትሮ ስለሚፍቀው የዓይን መስታወቱ ይቆስልና ጠባሳን ይፈጥራል። ይህም ሁኔታ ብርሃን ወደ ዓይናችን ውስጠኛው ክፍል መግባት እንዳይችል ስለሚያደርግ ዓይነስውርነትን ያስከትላል::

ይህ የትራኮማ መከላከያ ዘዴዎች ማስተማሪያ መምሪያ የተዘጋጀበት ዋና ምክንያት ህፃናት የተማሩትን ወደ ቤታቸው ከዚያም አልፎ ወደ አካባቢያቸው ይዘው በመሄድ የለውጥ ሐዋሪያ ሊሆኑ ይችላሉ በሚል መሠረተ ሀሳብ ነው::

ይህ የመምህሩ መምሪያ በመጀመሪያ በሔለን ኬለር ኢንተርናሽናል ድርጅት ለትምህርት ቤት ጤና አጠባበቅ መርሃ ግብር (School Health Program) የተዘጋጀው ሥርዓተ ትምህርት (Curriculum) ተጨምቆ የተተረጎመ ሲሆን የካርተር ሴንተር ኢትዮጵያ የትራኮማ ቁጥጥር መርሃ ግብር ከ1ኛ እስከ 4ኛ ክፍል ለሚገኙ ህፃናት እንዲስማማ አድርጎ ወደ አማርኛ ያስተረጎመውና ያቀነባበረው መምሪያ ነው::

ትራኮማ በአብዛኛው የግለሰብ ሳይሆን የአካባቢ ህብረተሰብ በሽታ እንደሆነ ተደርጐ ይቆጠራል:: ምክንያቱም ብዙ ሣይንቲስቶችና የተላላፊ በሽታ ኤክስፐርቶች የበሽታውን መተላለፍ ቢያውቁም በግለሰብ ደረጃ ሥርጭቱን መቆጣጠር አልቻሉምና ነው:: ስለዚህ በሽታውን ለማስወገድ የህብረተሰቡ የጋራ ተሳትፎና የተለያዩ የቁጥጥር ዘዴዎችን በመጠቀም መንቀሳቀስ ዋነኛው አማራጭ መፍትሄ ነው::

ታዲያ ህብረተሰቡ ትራኮማ የሚያስከትለውን ጉዳት /ዓይነ ስውርነትን/ ተገንዝቦ በሽታውን ለመቀነስ ብሎም ለማስወገድ በሚደረገው እንቅስቃሴ እንዴት ሊበረታታ ይችላል? ለዚህ ጥያቄ መልስ መስጠት የሚችሉት የህብረተሰቡ አካል የሆኑት የመንግሥት ሠራተኞች /የጤና፣ የትምህርት፣ የግብርና ባለሙያዎች ወዘተ/ እና በአጠቃላይም የበሽታው ተጠቂ የሆኑት የሕብረተሰብ ክፍሎች ይሆናሉ።

ካርተር ሴንተር - ኢትዮጵያ

# የመምህሩ መምሪያ ዋና ዋና ዓላማዎች

ይህ የመምህሩ መምሪያ መጽሐፍ የተዘጋጀበት ዋና ዓላማው የአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ ሣይክል መምህራን በመደበኛ የአካባቢ ሣይንስ ትምህርት ክፍለ ጊዜያቸው ስለትራኮማ እንዲሁም ስለመከላከያና መቆጣጠሪያ ዘዴዎች በማካተት እንዲያስተምሩ ነው። መጽሐፉ በአራት ምዕራፎች ለ12 ሰዓት የተመጠነ ሲሆን ባለሙያው አራቱን ክፍለ ትምህርቶች እንደ አመቺነቱ ከአንደኛ ክፍል እስከ ሦስተኛ ክፍል ላሉትና በተለይ ለአራተኛ ክፍል ተማሪዎች በህብረተሰብ ሣይንስ ስለጤና መታወክ ለሚሰጠው ትምህርት ድጋፍ እንዲሰጥ ተዘጋጅቷል። መምሪያው በተለይ /የትራኮማ ችግር ጉልቶ በሚታይባቸው/ አካባቢዎች በሽታውን እንዴት ለይቶ ማወቅ፣ መከላከልና ማከም እንደሚቻል ግንዛቤ ይሰጣል።

መምሪያው ስለትራኮማ በቂ ግንዛቤ በመስጠት መምህሩ ትምህርቱን እንዲያስጨብጥ ከማስቻሉ በተጨማሪ ከት/ቤት ውጭ ለሚገኙ ሌሎች የህብረተሰቡ ክፍሎችም ሥልጠና ለመስጠት ይረዳል።

በመምሪያው የተካተቱ ተግባራዊ ክንዋኔዎች /Activities/ የሚከተሉትን ቁልፍ ነጥቦች ከግንዛቤ በማስገባት ነው።

- *ለአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች አግባብ ያላቸው ተግባሮች*- በዚህ የመምህራን መምሪያ የተካተቱ ተግባሮችና እንቅስቃሴዎች ለልጆች አዝናኝና ፍላጎት የሚያሳድሩ እንዲሆኑ ተሞክሯል።
- *በት/ቤትና በማህበረሰቡ ዘንድ ያሉ ተቋሞችና እሴቶች*- ይህ መምሪያ በማህበረሰቡና በት/ቤቱ ያሉ ተቋሞችና እሴቶችን ባህሪያትና ተግባራትን ያበረታታል ።
- *የመምህሩን ፍላጎት ማገናዘብ*- መምሪያው የተለያዩ የማስተማር ዘዴዎችን ስላካተተ ስለትራኮማና ስለመከላከያ ዘዴዎች ማስተማር እንዲያስችል ሆኖ ቀርቧል።
- *የትራኮማ ቁጥጥር መርሃ ግብር ዓላማዎችና መልዕክቶች*- በመምሪያው የተካተቱ የትራኮማ ቁጥጥር መልዕክቶች በአጠቃላይ በትራኮማ ቁጥጥር ኘሮግራም በታቀፉ ማህበረሰብ ውስጥ ከሚተላለፉት መልዕክቶች ጋር የተዛመዱ እንዲሆኑ ተደርጓል።
- *መደበኛ ተማሪዎች በህብረተሰቡ የለውጥ ሀዋሪያነት*- ትምህርቱ ህፃናት ትራኮማን እንዴት እንደሚከላከሉ ከማስተማር በተጨማሪ ተማሪዎች ከትምህርት ሰዓት ውጭ የተማሩትን ለቤተሰቦቻቸው፣ ለጓደኞቻቸው እንዲሁም ወደ ት/ቤት ላልሄዱ የሕብረተሰብ ክፍሎች ጭምር በመንገር ስለ ትራኮማ በሽታ ግንዛቤ እንዲስፋፋ ያደርጋሉ።

ስለጤና ትምህርት ከመስጠት በተጨማሪ ስለ ህይወት ውጣ ውረድ በማስገንዘብ ተማሪው ከሚያጋጥመው ዕለታዊ ገጠመኞች በመነሳት የተለያዩ ክህሎቶችን (ነገሮች ማስተዋል፣ ማገናዘብ፣ መረዳት፣ ችግርን መቋቋም፣ መወሰንና ከሰዎች ጋር ተግባብቶ መኖር) እንዲያዳብሩ ታስቧል።

## የመምህሩ መምሪያ አጠቃቀም

ይህ የማስተማሪያ መምሪያ በማውጫው እንደተጠቀሰው በአራት ክፍለ ትምህርቶች የተከፈለ ነው። እያንዳንዱ ክፍለ ትምህርት የራሱ የሆነ ግብና ዝርዝር አላማዎች ሲኖሩት የየራሳቸው ድርጊቶች (Activities) ደግሞ ተማሪዎች እንዲረዷቸው በየክፍለ ትምህርቱ መጀመሪያ ተዘርዝረዋል። ድርጊታዊ ክንዋኔዎች የሚሰሩበት የጊዜ ርዝመት ከአምስት ደቂቃ እስከ አንድ ሰዓት የተሰጠ ስለሆነ መምህሩ ይህን ተገንዝቦ አመቺውን እንቅስቃሴ በጊዜውና በቦታው መጠቀም ይጠበቅበታል። የትምህርቱ አዘገጃጀት አንዱ በአንዱ ላይ መሰረት ያደረገ በመሆኑ ማለትም ክፍል ሁለት በክፍል አንድ ላይ፣ ክፍል ሦስት በክፍል ሁለት ላይ፣ ክፍል አራት በክፍል ሦስት ላይ፤ የክፍለ ትምህርቱ ምዕራፍ አቀማመጥ ቅደም ተከተሉ ሣይዛባ መሰጠት ይኖርበታል። ሆኖም መምህሩ ትምህርቱን ሲያስተምር እንደሚቀርበው የክፍል ደረጃ ወይም አድማጭ ትምህርቱን በቀላሉ ዘዴ ወይም በጠለቀ ዘዴ ሊያቀርብ ይችላል። በየክፍለ ትምህርቱ ንዑስ ክፍለ ትምህርት መጨረሻ ለመምህሩ የተተወ ክፍት "የመምህሩ ማስታወሻ" የሚል ተሰጥቷል። በዚህ ቦታ መምህሩ ይጠቅመኛል ብሎ ያሰበውን የራሱ ማስታወሻና የተደረጉትን እንቅስቃሴዎች ውጤት ማስታወሻ መፃፍ ይችላል።

መምሪያው የራሱ ድርጊታዊ እንቅስቃሴ (Activities) ቅጽ (ተቀጽላ አንድ ይመልከቱ) አለው። መምህራን በየክፍለ ትምህርቱ መጨረሻ ሥራቸውን ቢገመግሙበት ጥቅሙ ከፍተኛ ይሆናል። የዚህ ቅጽ ዓላማ ትምህርቱ ለስንት ተማሪዎች፣ በምን ዝርዝር ይዘቶች (content) እንደተሰጠ፣ የማስተማሪያ ዘዴዎች አጠቃቀም፣ የትምህርት አቀራረቡ ድክመትና ጥንካሬ ምን እንደነበረ ለወደፊቱ መሻሻል ስላለባቸው ጉዳዮች ለመገንዘብ ይረዳል። በተለይ የዚህ ዓይነቱ መረጃ መኖር ለተጓዳኝ ት/ቤቶች (cluster schools) ርዕሰ መምህራንና መምህራን እርስ በርሳቸው እንዲማማሩበት ከፍተኛ እገዛ ያደርጋል።

በተጨማሪ ይህ የማስተማሪያ መምሪያ በጥቂቱም ቢሆን ስለተጠቀመባቸው የማስተማሪያ ዘዴዎች ፍንጭ በቀጣዩ ክፍል አሳይቷልና ይመልከቱ።

## የትራኮማ በሽታን ለመከላከልና ጤናን ለማስፈን ልጆች የሚጫወቱት ሚና

ይህ የጤና ትምህርት የማስተማሪያ መምሪያ አዘገጃጀት ያተኮረው በጤናው ትምህርት ዘርፍ ላይ «ልጆች ለልጆች» (Child to Child) በሚል መርህ ላይ ተመሥርቶ ነው:: አቀራረቡ ልጆች የቀሰሙትን ዕውቀት በየጊዜው ለጓደኞቻቸው፣ ለቤተሰቦቻቸው እንዲሁም ለአካባቢው ህብረተሰብ እንዲያስተላልፉ ይረዳል:: ለዚህ መርህ መነሻው ምክንያት የጤና ጉዳይ የሁሉም ጉዳይ መሆንና ለጥቂት የጤና ባለሙያዎችና ዶክተሮች ብቻ የሚተው አለመሆኑ ነው:: ልጆች እንደሌሎቹ የህብረተሰቡ ክፍሎች /ወጣት፣ ጎልማሳ፣ሽማግሌ፣ አሮጊት ወዘተ/ የራሳቸውን ንፅህና በመጠበቅና ለሌሎችም አርአያ መሆን ይጠበቅባቸዋል:: ቀጥሎ በሣጥን ውስጥ የተመለከተው ማብራሪያ «Child to Child» ከሚል ማስተማሪያ መጽሐፍ በአውሮፓውያን አቆጣጠር በ1992 በግራዚያንና ሁግ ከተፃፈው የተወሰደ ነው::

### ልጆች ስለጤና ያላቸውን ግንዛቤና ልምድ ለሌሎች እንዴት ያሰራጫሉ?

ልጆች ስለ ጤና ያላቸውን ዕውቀት ለሌሎች ለማስተላለፍ የተለያዩ መንገዶችን ሊጠቀሙ ይችላሉ:: እነርሱም ፤

1. *<u>በእድሜ ትልቅ የሆኑ ልጆች ታናናሾቻቸውን ይረዳሉ</u>*፤ ታናናሾቻቸውን ይንከባከባሉ፣ ያስተምራሉ፣ የጤናማ ሰው ባህሪ በማሳየት ተምሳሌት ይሆናሉ።
2. *<u>ልጆች የዕድሜ አቻ ጓደኞቻቸውን ይረዳሉ</u>*፤ አብረው በመስራት እርስ በርሳቸው ይማማራሉ። ወደ ት/ቤት በመሄድ የመማር ዕድል ያገኙ ልጆች ዕድሉን ላላገኙት ዕርዳታ ይሰጣሉ።
3. *<u>ልጆች ስለጤና ያላቸውን ዕውቀትና ግንዛቤ ለቤተሰቦቻቸውና ለአካባቢው ህብረተሰብ ያስተላልፋሉ</u>*፣ በተለይ በትምህርት ቤት የተማሩትን አይዘነጉም:: ለምሳሌ ሶስና በትምህርት ቤት ስለ ትራኮማ በሽታ ምልክቶችና ስለ መድሃኒቱ /ቴትራሳይክሊን/ በመንገሯ እናቷ ታናሽ ወንድሟን ወደ ሃኪም ቤት በመውሰዷ ታክሞ ሊድን ችሏል:: በተጨማሪም ሶስና አይነ ምድርን በጉድጓድ በመፀዳዳት የትራኮማ በሽታን መከላከል እንደሚቻል በማሳየቷ ቤተሰቦቿ የመፀዳጃ ጉድጓድ ቆፍረው ሽንት ቤት በመስራት መጠቀም ችለዋል:: በተመሳሳይ ሁኔታ እንዲሁ ከአካባቢው ህብረተሰብ ጋር በመተባበር የጤና ኮሚቴ ተቋቁሞ የህዝብ ሽንት ቤት በጋራ ተሰርቶ አገልግሎት መስጠት ጀምሯል::

የዚህ ማስተማሪያ መምሪያ አዘጋጅ ልጆች ለልጆች ( Child to Child) የሚለውን መሰረታዊ ሀሳብ ለመተግበር፣

- ልጆች በቀጥታ ተሳትፎ አዲስ ክህሎትና ዕውቀት እንዲያገኙ የትምህርቱን አቀራረብ በቀልድና በጨዋታ መልክ እንዲሆን አድርገዋል::
- የጤና ትምህርት በት/ቤቶች በአዲሱ የትምህርት አቀራረብ መሠረት ተማሪ-ተኮር (Student-Centered) ለማድረግ መምህሩ ብቻ ተናጋሪ ተማሪው አድማጭ እንዳይሆን ተማሪው የሰማውን በተግባር ማሳየት እንዳለበት (የራሱን ንፅህና ከመጠበቅ ጀምሮ) ለሌሎችም መናገር የሚያስችለው እንዲሆን አድርገዋል::
- ልጆች ለራሳቸው ጥሩ ሥራ ሲሰሩ ለሌሎችም አርአያ መሆናቸውንና ከሌሎችም ጋር አብሮ ለመስራት እንዲበረታቱ ማስቻሉን አሳይተዋል::

## የትራኮማ በሽታን በመከላከልና ጤናን በማስፈን የመምህራን ሚና

- የጤና ትምህርት ዕውቀትን ከማስተላለፍ በተጨማሪ መምህራን በጥሩ ሥነ ምግባር የታነፁና ለልጆች መልካም አርአያ መሆን፣
- ልጆች በሚሠሩት ጥሩ ሥራ ማበረታታት፣
- በትምህርት ቤቱ የሰንደቅ ዓላማ ሥነ ሥርዓት ተገኝቶ ማክበር፣
- ስለ አይናችን ጤንነት፣ ስለ ትራኮማ በሽታና የመከላከያ ዘዴ ከሚመለከታቸው የጤና ባለሙያዎች ጋር በፈቃደኝነት አብሮ ለመሥራት መንቀሳቀስ /መሥራት፣
- ልጆች በክፍል ውስጥ የራሳቸውን ፈጠራ ተጠቅመው ድራማ እንዲያዘጋጁ ማትጋት /ማገዝ ይጠበቅባቸዋል።

## ይህን የመምህራን መምሪያ ለመተግበር የሚያግዙ ሥልቶች

### 1. ክለሳ (review) እና የቅድመ ትምህርት ዝግጅት (Preparation) ጠቀሜታ

ትምህርት ቤትና ህብረተሰቡ ከመምህራን ብዙ ነገሮችን ይጠብቃል። በዚህም መሠረት መምህሩ ትምህርቱን ለማጠናቀቅ የተመደበለትን ጊዜና ማቴሪያል ያላገናዘቡ አስተያየቶች ይሰነዘራሉ። ይህን ማስተማሪያ መምሪያ መጽሐፍ ያዘጋጀው ክፍልም በግልፅ የመምህሩን ሥራ ሚና ቢረዳም፣ መምህሩ ባለው ጥቂት ጊዜ ስለትራኮማ በሽታ በዝግጅቱ ውስጥ በማካተት ያለፈውን ትምህርት በመጠኑ በመከለስና ለሚቀጥለው ትምህርት ቅድመ ዝግጅት በማድረግ ትምህርቱን በክፍል ውስጥ በመስጠት ከንድፈ ሀሳብ ወደ ተግባር በተቻለ ፍጥነት በመለወጥ ውጤታማ ማድረግ ይችላል ብሎ ያምናል።

## 2. አነስተኛ የቡድን ሥራ (ከጓደኛ ጋር ተባብሮ መሥራት)

ይህ የመምህራን መምሪያ የግላዊ ግንኙነት (Interpersonal relationship) ክህሎትን ልጆች አዳብረው በግልና በቡድን ከጓደኞቻቸው ጋር እንዲማማሩ መምህራን መድረኮችን እንዲያዘጋጁ ይረዳል:: ይህን ሀሳብ ‹‹ልጆች ለልጆች›› / Child to Child/ የሚለው መጽሐፍ ሲገልፅ በጋራና በግል ስለ ጤና ፕሮጀክት መወያየትና መሥራት ልጆችን ለሥራ እንደሚያበረታታ፣ ሀሳባቸውን በነፃ እንዲያንሸራሽሩ እንደሚረዳ፣ ልዩነቶችን አስወግደው በውይይት እንዲተማመኑና የጋራ ግንዛቤ እንዲፈጥሩ፣ የራሳቸው ምርጫና ውሳኔ ላይ እንዲደርሱ የሚጋብዝ መሆኑን አስቀምጧል::

ከላይ የተመለከተውን «ልጆች ለልጆች» የሚለውን መጽሐፍ ሀሳብ በማስፈን ተማሪ ተኮር (Student-Centered) ትምህርት ለመተግበር ቀጥሎ የተመለከቱትን መረዳት ይጠቅማል::

- ለመጀመሪያ ጊዜ ልጆች በቡድን ለመሥራት እንዲችሉ አምስት ወይም ስድስት ልጆች ያሉበትን ቡድን ሳትራራቁ በተቀመጣችሁበት አካባቢ ቡድን መስርቱ ተብለው ጥቂት ደቂቃ ቢሰጣቸውና እንዲሰሩ ቢደረግ እያንዳንዱ አባል የቡድኑን አባላት ስም ሊያውቅ ይችላል::
- ለቡድኑ ሥራ የተወሰነ ሰዓት በመመደብ ሥራው በተሰጠው የጊዜ ገደብ መጠናቀቁን ክትትል ማድረግ::

- የቡድን ሥራውን በሚሰሩበት ወቅት ዲሲፕሊንን በተከተለና ካለ ምንም ጫጫታ እንዲሆን መግለጽና ከየቡድኑ አልፎ አልፎ ፀጥታ የሚነሱ ካሉም እነሱን ለይቶ ለጊዜው ለብቻቸው እንዲሰሩ ማድረግ::
- መምህሩ ተማሪዎች የቡድን ሥራ ሲሰሩ ዝም ብሎ መቀመጥ የለበትም:: እየተዟዟረ የተሰጠውን ሥራ በአግባቡ መሥራታቸውን መከታተልና ጥያቄዎችም ካሉ ተገቢውን ምላሽ በመስጠት መርዳት ይኖርበታል::
- በአንዳንድ የቡድን ሥራ ለምሳሌ ቲያትር ነክ የሆነ እንደሆነ ተሳታፊዎች የሚያደርጉትን ሥራ የሚያስተባብሩ ፀሐፊ፣ ጊዜ ተቆጣጣሪ፣ ወዘተ የመሣሰሉ ሥራዎችን ማከፋፈል ይገባዋል::

## 3. ሥዕሎችንና የትረካ መጽሐፍትን መጠቀም

«ልጆች ለልጆች» በሚለው መጽሐፍ እንደተመለከተው ሥዕሎች ልጆች ያሉበትን ወቅትና ሁኔታ ካላቸው ግንዛቤ ጋር አዛምደው እንዲመለከቱ ይረዳቸዋል:: ስለ ሥዕሉ ቴክኒክ ለመረዳት ቀላሉ ዘዴ ሥዕሉን ለልጆቹ ለረዥም ጊዜ በማሳየት ከሥዕሉ ምን ሀሳብ እንዳገኙ መጠየቅና ያላቸውን ሀሳብ ተናግረው እስከሚያበቁ ማድመጥ፤ በዚሁ አይነት ለሌሎችም የመናገር ዕድል በመስጠት ሀሳቦችን መቀበልና የሚቻል ከሆነ ስለተመለከቱት ሥዕል በቲያትር መልክ እንዲያቀርቡ መጠየቅ:: በተለይ ስዕሎቹ ተከታታይ ታሪክ ያላቸው ከሆነ ተማሪዎቹ የእያንዳንዱን የሥዕል ገጽ በተገቢው ርቀትና መጠን የተፃፉ መግለጫዎችን በራሳቸው ፍጥነት አንብበው መረዳታቸውን ለመጀመሪያ ጊዜ ማረጋገጥ ይገባል:: ልጆችም የራሳቸውን ሥዕል ለመሣል እንዲችሉ ማበረታታትና የሰውን ሞዴል ኮፒ እንዳያደርጉ መምከር፤ ስለ ሥዕላቸውም ምን መልዕክት እንዳለው ለሌሎች እንዲያስረዱ ማበረታታት ጥሩ ነው:: ምክንያቱም ሥዕሎች ከቃላት የበለጠ መልዕክት ማስተላለፍ ይችላሉና::

## 4. የተማሪዎችን ድርሰት መጠቀም

ልጆች የራሳቸውን ወጥ የሆነ ድርሰት ከትምህርቱ ጋር አያይዘው እንዲጽፉ ማድረግና የተመረጡ ድርሰቶችን በክፍል ውስጥ ማስነበብ ወይም በቡድን እንዲያነቡ በማድረግ የሰሙትን ድርሰት በክፍል ውስጥ ብቻ ሣያስቀሩ ከክፍል ውጭም እንዲያሰሙ ማድረግ::

## 5. ልዩ ልዩ ጨዋታዎችን መጠቀም

ለልጆች በጨዋታና በቀልድ መልክ ብዙ ትምህርት ማስተላለፍ ይቻላል:: ስለ ትራኮማ መከላከል ልዩ ልዩ ጨዋታዎችን በማስተማሪያ ዘዴዎች የመጠቀም ሥርዓት በቤት ውስጥ ከወንድሞቻቸውና እህቶቻቸው ጋር እንዲሁም ወደ ት/ቤት ከማይሄዱ ጓደኞቻቸው ጋር እነዚህኑ ጨዋታዎች ደግመው እንዲጫወቱ ስለሚያደርጋቸው በሽታውን የመከላከል አድማስን ማስፋት ይቻላል።

## 6. ድራማን መጠቀም

ልጆች ድራማን በመጠቀም ስለ ትራኮማ በሽታ ትምህርታዊ መልዕክት ለራሳቸውም ሆነ ለሌሎች ማስተላለፍ ይችላሉ:: በተለይ የልጆች ድራማ በአካባቢው ለሚገኙ ጉልማሶች ከት/ቤት ውጪ አዘጋጅቶ ማቅረብ ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል::

ልጆች ለልጆች (Child to Child) በሚለው መጽሐፍ እንደተመለከተው ድራማን ስናዘጋጅ የሚከተሉትን ነጥቦች ማጤን አለብን::

- በድራማው ውስጥ ያለው የጤና ትምህርት መልዕክት ምንድን ነው ብሎ መወሰን::
- ገፀ-ባህሪያትን ለይቶ ማስቀመጥና መመደብ::
- ልጆች በድራማው ምን ዓይነት አልባሳት (ጭንብል) መጠቀም ይኖርባቸዋል? አሻንጉሊትና ሌሎች ምን ነገሮች ያስፈልጓቸዋል? ብሎ ማሰብ
- ድራማው እንዴት ባለ ልብ ሰቃይ (አንጊ) ታሪክ ይደምደም?
- የእያንዳንዱን የድራማው ክፍል ገፀ-ባህሪ እነማን ይጫወቱ?
- በክፍል የቀረበው ድራማ ለህብረተሰቡ እንዴት፣ መቼና የት መቅረብ አለበት ብሎ የተሻለ ጊዜና ቦታ ለመወሰን የተመልካችን ሀሳብ መቀበል::

ልጆች ድራማቸውን ለህብረተሰቡ የሚያቀርቡ ከሆነ ዝግጅታቸውን በት/ቤቱ አዳራሽ ወይም ሰፋ ያለ ክፍል (ቦታ) ወስደው መለማመድና ማቅረብ ይኖርባቸዋል:: ምክንያቱም በክፍል ውስጥ ያቀረቡት ዝግጅት ብቻውን በተለያዩ ምክንያቶች በቂ አይሆንምና::

## 7. ወደ ህብረተሰቡ በመሄድ ያሉትን ችግሮች መገምገምና አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ

በማስተማር እንቅስቃሴ ተማሪዎች ስለ ትራኮማ በሽታ መንስኤ ማስተዋልን (Observation) ለሚመለከታቸው ክፍሎች ቃለ መጠይቅ ማድረግን (Interview) እንደዚሁም ሕብረተሰቡ በሽታውን ለመከላከል በሚያደርገው እንቅስቃሴ ውስጥ

መሳተፍን የሚጋብዝ የማስተማር እንቅስቃሴ ለልጆች ከፍተኛ ግንዛቤን ያስጨብጣል:: ስለሆነም በዚህ የመምህራን መምሪያ ተማሪዎች ከህብረተሰቡ ጋር የሚሳተፉበት የተለያዩ ዘዴዎች ስላሉ መምህራን የሚከተሉትን ነጥቦች ከግምት ውስጥ በማስገባት መንቀሳቀስ ይኖርባቸዋል::

- በምን ያህል የጊዜ ገደብና መቼ ወደ ህብረተሰቡ መኬድ እንዳለበት
- ተማሪዎች ዝግጅታቸውንና ልምዳቸውን በጥንቃቄ እንዲሰሩ ለህብረተሰቡም ከበሬታ እንዲያሳዩ፣ ህብረተሰቡ የሚቀበላቸውንና የማይቀበላቸውን ባህላዊ እሴቶች ለይተው እንዲያውቁ ማስገንዘብ
- ለአካባቢው አስተዳዳሪዎች፣ ጤና ባለሙያዎችና ነዋሪዎች ተማሪዎች ወደ ህብረተሰቡ የመጡት ስለትራኮማ በሽታ አንዳንድ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ስለሆነ አስፈላጊውን መረጃ በመስጠት እንዲተባበሩ ማሳወቅ። ወደ ህብረተሰቡ ስንሄድ ህብረተሰቡ የትራከማ በሽታን ለመከላከል ያደረገውን እንቅስቃሴ ጠንካራና ደካማ ጐን ለይተን ለታዩት ድክመቶች የራሳችንን መፍትሄ በዕለታዊ ክንዋኔ (action plan) ማስቀመጥ ይኖርብናል:: ከዚህ ቀጥሎ የተመለከተው ዕለታዊ ዕቅድ እንደ ሞዴል ሊወሰድ ይችላል:: ሞዴሉን መምህራንና ተማሪዎች በጥያቄና መልስ መልክ አብረው ያዘጋጁት ነው::

## የዕለታዊ ዕቅድ ናሙና

<table>
<tr><td>የታዩ ችግሮች</td><td colspan="2">በጐረቤቶቻቸው አካባቢ የሚገኙ ልጆች ዘወትር በአቧራ ስለሚጫወቱና ፊታቸውን ስለማይታጠቡ የፊታቸው ገፅታ የቆሸሸ ነው::</td></tr>
<tr><td>መወሰድ ያለበት እርምጃ</td><td colspan="2">ውሃ /በባልዲ፣ በፕላስቲክ ወዘተ/ ልጆች በሚጫወቱበት አካባቢ በመወሰድ የሚጫወቱትን ልጆች ወደ ውሃው እንዲመጡ በመጠየቅ እኛ ተማሪዎች ፊታችንን መታጠብ እንዴት በቀላሉ በት/ቤት እንደጀመርን በማሳየት እንዲታጠቡ መጋበዝ</td></tr>
<tr><td>የእርምጃው ውጤት</td><td colspan="2">ትንንሽ ልጆች ቢያንስ በቀን አንድ ጊዜ ፊታቸውን ሊታጠቡ ይችላሉ:: እንዲሁም ትክክለኛውን የፊት አስተጣጠብ ቴክኒክ ይገነዘባሉ::</td></tr>
<tr><td>መቼ? በቀን ስንት ጊዜ ማድረግ እንችላለን?</td><td colspan="2">በየዕለቱ ከሰዓት በኋላ ስንጫወት የሚጫወቱትን ልጆች ፊት ገጽታ በማየት ንፅህናቸው ያልተሟሉ ካሉ ማረም</td></tr>
<tr><td rowspan="3">በየደረጃው ምን ዓይነት እርምጃ መወሰድ አለበት? ምን ምን ማድረግ ይጠበቅበታል?</td><td>1. ተጨማሪ የውሃ መያዣ /ባልዲ፣ ፕላስቲክ ወዘተ/ ይኑርህ/ሽ</td><td>ዘነብ እናቷ ያላቸውን ባዶ የዘይት ጣሳዎችና ባልዲዎችን መዋስ ትችላለች</td></tr>
<tr><td>2. ውሃ እየቀዳህ ዘወትር ልጆች ወደሚጫወቱበት ቦታ ውሰድ ላቸው</td><td>በየተራ ውሃ እንቀዳለን ሰኞ ዘነብ፣ ማክሰኞ ኢያዩ ወዘተ</td></tr>
<tr><td>3. ልጆች ፊታቸውን እንዴት መታጠብ እንዳለባቸው ታጥበህ አሳይ ካልቻሉም ፊታቸውን አጠብላቸው፣ እንደ ትልልቅ ልጆችም እንዲታጠቡ አበረታቱዋቸው</td><td>ሁላችንም</td></tr>
</table>

| | |
|---|---|
| ማን ይረዳናል? | ታላላቅ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ይረዱናል፣ ለዘመዶቻችን ምን እንደምንሰራ ከገለጽንላቸው ሊረዱን ይችላሉ:: |
| እንዴትና መቼ ሥራችንን እንገመግማለን? | በመጀመሪያው ቀን ልጆች ተጫውተው ወደ ቤታቸው ሲመለሱ የስንቶቹ ፊት ቆሻሻ እንደነበረ እንቆጥራለን:: በማከታተልም ከጨዋታው በፊትና በኋላ ያለውን እንመዘግባለን:: ከአንድ ወር በኋላ ደግመን ስንት ልጆች በራሳቸው ጥረት ፊታቸውን መታጠብ እንደጀመሩና እንዳልጀመሩ መረዳትና ለቀጣይ ርምጃ መዘጋጀት:: |

# የትራኮማ በሽታን ለማስወገድ የተዘጋጀ የጤና ትምህርት ፕሮግራም

| የየክፍለ ትምህርቱ ግብ (Objectives) | ቀልፍ መልዕክቶች (Key Messages) | ቀልፍ እንቅስቃሴዎች (Key activities) | የማስተማሪያ መርጃ (Instructional materials) |
|---|---|---|---|
| 1. የማየት ጥቅም /የዓይን ጥቅም/<br>1.1 ተማሪዎች የዓይነ ስውራን ሰዎችን ስሜት ይጋራሉ /ይገነዘባሉ ያለማየትን ችግር ይረዳሉ።<br>1.2. ተማሪዎች ስለ ጤናማ ዓይን አድናቆት ይኖራቸዋል።<br>1.3 ተማሪዎች የተለያዩ የዓይን ውጫዊ ክፍሎችን ይረዳሉ። | "የዓይኔ ብርሃን ለኔ ወሳኝ ነው" | - ዓይናችንን በመሀረብ ሸፍኖ ጨረቃ ጨረቃ እያሉ እያጨበጨቡ አለንጋ የመጋረፍ ጨዋታ መጫወት<br>- ተማሪዎች በአካባቢያቸው ከሚገኙ ዓይነ ስውራን ሰዎች ጋር ስለ ዓይን ብርሃን ማጣት ችግሮች መጠይቅ ማድረግ | - መሐረብ<br>- ማየት የተሳነው ሰው ሥዕል<br>- የዓይን ክፍሎችን የሚያሳይ ፖስተር ወይም ቻርት<br>- የተለያዩ ከለር ያላቸው እርሳሶች |
| 2. ስለ ትራኮማ በሽታ፡ ምንድን ነው? እንዴት ይይዘናል? ከትራኮማ የሚመጣ ዓይነ ስውርነትን ስለ መከላከል፡<br>2.1. ተማሪዎች የትራኮማን በሽታ ደረጃዎች ዓይን መቆርቆር (Active trachoma) ዓይነ ፀጉር (Trichiasis) እናም ዓይነ ስውርነት (Blindness) ይለያሉ።<br>2.2. ተማሪዎች የትራኮማን ምልክት መለብለብን (Active Trachoma) እና ዓይነ-ፀጉር (Trichiasis) ምልክቶች ጠንቅቀው ይረዳሉ።<br>2.3. ተማሪዎች የመተላለፊያውን መንገድ / ከሰው ወደ ሰው እንዲሁም ከዝንቦች በእጅ ጣት፣ የእጅ መሐረብን በጋራ በመጠቀምና ወዘተ / መሆኑን መናገር ይችላሉ።<br>2.4. ተማሪዎች ትራኮማ የሚያስከትለውን ጉዳት ለመከላከል እንደሚቻልና ለመከላከል የሚቻልባቸውን አራት <<የ ማ መ ን >> ዘ ዴ ዎ ች ን ( S A F E Strategies ይረዳሉ።<br>2.5. ተማሪዎች ወጣቱ ትራኮማን በመከላከል የበሽታው መስፋፋት እንደሚገታ ይገነዘባሉ። በሽታውን ለመከላከል የመተላለፊያው መንገድ የሆኑ ንክኪዎችን በማቋረጥ ለማረጋገጥ ይችላሉ። | - የማያሳክክ ትራኮማ ወደ ዓይነ ፀጉር (Trichiasis) ሊሸጋገር ይችላል<br><br>- ከትራኮማ የሚመጣ ዓይነ ስውርነትን እንዴት እንከላከል <<ማመን>> SAFE) መርህ በማድረግ<br><br>- ትራኮማን ለመከላከል የሚቻ ለው በ <<ማመን>> ዘዴዎችን (SAFE Strategies) ነው። | - ዓይነ ስውራን ሰዎች ቁጥር ከዕለት ወደ ዕለት እየጨመረ በመምጣት ላይ እንደሚገኝና የመተላለፊያ ዘዴውንና መፍትሄውን የሚገልጽ ጽሑፍ ለክፍል ማንበብ<br><br>- የ <<ማመን>> (SAFE) ሥራን ለመተግበር ስትራቴጂዎቹን ማስቀመጥ<br><br>- ማስቆረጥ (Surgical Correction)<br>- መድሃኒት (Antibiotic)<br>- ንፁህ ፊት (Facial Cleanliness)<br>- ንፁህ አካባቢ (Environmental Sanitation) | -ስለ ትራኮማ የሚገልጽ ጽሑፍ /የተረት መጽሐፍ/<br><br>-ወደ ዓይነ ስውርነት የሚያመራውን የዓይን ማዝ የሚያሳይ የትራኮማ ፖስተር/ስዕል<br><br>-ወረቀትና እርሳስ የስዕል መቀበያ ከለር |

| | | | |
|---|---|---|---|
| **3. የትራኮማ መስፋፋትና የመከላከያ ዘዴዎች**<br>3.1. ተማሪዎች ትራኮማ የሚተላለፍባቸው መሰረታዊ መንገዶች ማለትም ከሰው ወደ ሰው በእጅ ጣቶች የጋራ የእጅ መሐረብ በመጠቀም፣ በዝንቦች፣ በጋራ የአይን መድሐኒት ቲዩብ በመጠቀም (በሁለተኛው ክፍል ትምህርት የተሰጠውን ያስታውሳሉ)።<br>3.2. ተማሪዎች ስለ ትራኮማ በሽታ መተላለፊያ መንገዶች የነበራቸውን እምነትና ትክክለኛ ውን ሁኔታ ለይተው ይረዳሉ።<br>3.3. ተማሪዎች ትራኮማ በሽታን የሚያፋጥኑ ወይም የሚገቱ ሁኔታዎችን መለየት ይችላሉ። የፊት መቆሸሽ፣ ቆሻሻ ልብስ፣ የሰው ዓይነ ምድር ወይም ቆሻሻ ለተባይ መራቢያ ምቹ ቦታ መሆኑን ይረዳሉ (በሁለተኛው ክፍል ትምህርት የተሰጠውን ያጠናክራሉ)።<br>3.4. ተማሪዎች ስለ ቆሻሻ የፊት ገጽታና አካባቢ ጥላቻና በተቃራኒው ስለ ንፁህ የፊት ገጽታና አካባቢ አድናቆት ይኖራቸዋል።<br>3.5. ተማሪዎች በግላቸው ከቤተሰቦቻቸውና ከህብረተሰቡ ጋር በመሆን የትራኮማ በሽታን ለመከላከል እንደሚቻል ያረጋግጣሉ። ያስረዳሉ። | - ትራኮማ ከሰው ወደ ሰው እንዴት ይተላለፋል?<br><br>- የቆሸሸ ፊት እጅና ልብስ እንዲሁም ዝንቦች የትራኮማ በሽታ በቀላሉ ከሰው ወደ ሰው እንዲተላለፍ ያደርጋሉ።<br><br>- የቆሸሸ የፊት ገጽታና ልብስ የትራኮማን በሽታ ያባብሳል። በተቃራኒው ንፁህ የፊት ገጽታ፣ ንፁህ መሐረብና ንፁህ የመኖሪያ አካባቢ የትራኮማን በሽታ መከሰት ይገታል።<br><br>- <<ማመን>> (SAFE)<br><br>- ማስቆረጥ (Surgical Correction)<br>- መድሃኒት (Antibiotic)<br>- ንፁህ ፊት (Facial Clean)<br>- ንፁህ አካባቢ (Environ. Sanit.) | - የትራኮማ በሽታ እንዴት እንደሚተላለፍ የሚያሳየውን ሥዕላዊ መጽሐፍ በማየት ገፀባህሪውን መጫወት<br><br>- በዓይን የሚታዩ ቆሻሻዎችንና ጤናማ ሁኔታ ችግር የሚፈጥሩትን ነገሮች መለየት<br><br>- ተማሪዎች በጋራ በመሆን ስለ ትራኮማ በሽታ መነጋገር መፍትሄም መስጠት (የፊት ገጽታን መታጠብ የእጅ መታጠብንና ከመኖሪያ ቤት አካባቢ ርቆ በሽንት ቤት መፀዳዳት) | - የተማሪዎችን የተለያየ ገፀ ባህሪ የሚያሳይ ሥዕላዊ የቃላት ስሌዳ በመምህሩ የተሰራ<br><br>- ቆሻሻንና የቆሻሻ አካባቢ የሚያመለክቱ የተለያዩ ምሥሎች<br><br>- ወረቀት እርሳስና የተለያዩ ከለሮች ልጆች ስዕል የሚሰሩበት |
| **4. የትራኮማ ቀንን ስለማቀድ** | | - በትራኮማ በሽታ መከላከያ ዕለት የሚቀርቡ ፕሮግራሞችን በቅድሚያ መምረጥ<br><br>- በአካባቢው ለሚገኙ አስተዳዳሪዎች፣ የጤና ባለሙያዎችና በጎ ፈቃደኞች ኃላፊነት በመስጠት ፕሮግራሞችን በቅንጅት ማዘጋጀት | |

## ክፍለ ትምህርት አንድ

### የማየታችን አስፈላጊነት

**ቁልፍ መልዕክት:**

**«የዓይኔ ብርሃን በጣም ያስፈልገኛል»**

## የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች

1. ተማሪዎች ማየት እንደተሳናቸው በማስመሰል የዓይነ ስውራን ሰዎችን ስሜት (ጉዳት) ይገነዘባሉ::
2. ተማሪዎች ስለ ጤናማ ዓይኖች በጎ አመለካከት ይኖራቸዋል፣ ለአይናቸው ትልቅ ዋጋ ይሠጣሉ::
3. ተማሪዎች የዓይንን የተለያዩ ክፍሎች መግለፅና ማብራራት ይችላሉ::

## ተግባራት (Activities)

1. አጭር ገለፃ (ለአምስት ደቂቃ)
2. ዓይነ ስውራን ሰዎችን ማስመሰል (ለአንድ ሰዓት)
3. በቡድን የሚሠራ "ዓይነ ስውራን በሕብረተሰባችን ወስጥ" (እስከ ስድሣ ደቂቃዎች)
4. በህብረተሰቡ ውስጥ ከሚኖሩ "ዓይነ ስውራን ስዎች ጋር ቃለ ምልልስ ማድረግ (እስከ ስድሣ ደቂቃዎች)
5. የዓይን ክፍሎችን መሣል (ለሠላሣ ደቂቃዎች)

ሙሉውን ክፍለ ትምህርት ለመጨረስ የሚወስደው ጊዜ ከሦስት ስዓት በላይ ነው::

## 1. መግቢያ

የተሰጠው ጊዜ : አምስት ደቂቃ

የትምህርት መረጃ መሣሪያዎች: የዓይነ ስውር ሰው ምስል

አቀራረብ: ከማስተማርህ/ርሽ በፊት የሚደረጉ ድርጊቶችን /activities/ ማንበብ

1.1. መምህር የአንድ ዓይነ ስውር ሰው ፎቶግራፍ (ምስል) ካሳዩ በኋላ ተማሪዎቹን የሚከተሉትን ጥያቄዎች መጠየቅ «ይህን የሚመስል ሰው ተመልክታችሁ

ታውቃላችሁ? ምን የደረሰበት ይመስላችኋል?» ከዚህ በተጨማሪ ዓይነ ስውርነት ምን እንደሚመስል የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ መልሳቸውን በቃል መቀበል:: «ዛሬ ስለማየት እንነጋገራለን:: ማለትም ዓይናችንን እንዴት እንደምንጠብቀው፣ ማየት ለእኛ ምን ማለት እንደሆነ፣ ማየት ቢሳነን ኑሮ ምን ያህል ከባድ ሊሆን እንደሚችል እናስተውላለን:: ማየት ቢሣናችሁ ኑሮ ምን ሊመስል እንደሚችል በህይወታችሁ አሰባችሁ ታውቃላችሁ? ምን የሚመስል ይመስላችኋል? መምህር የተማሪዎችን አስተያየት ይጠይቁ::»

**2. የማስመሰል ጨዋታ (Empathy game)**

የተሰጠው ጊዜ: 60 ደቂቃ

የትምህርት መርጃ: የአይን መሸፈኛ ሪቫን የእጅ መሐረብ ወይም ቁራጭ ጨርቅ (የሚያሳይ)

አስፈላጊ ዝግጅት: መምህር ከማስተማርዎ በፊት ሙሉ ተግባራዊ ክንዋኔዎች /Activities/ በሚገባ ያንብቡ:: ከሁለቱ አማራጭ የማስተማሪያ መንገዶች አንዱን የሚመችዎን ይምረጡ:: የአይን መሸፈኛው ሪባን ከሙከራው በኋላ በሚገባ መታጠብ ይኖርበታል ምክንያቱም ለትራኮማ መተላለፊያ መንገድ ነውና::

## *አማራጭ አንድ*

ሀ. መምህር ተማሪዎችን ከክፍል ወደ መጫወቻ ሜዳ ከወሰዱ በኋላ ተማሪዎቹ በሁለት ጥንድ ምድቦች (Pair) እንዲከፈሉ ይደረጋል:: አንደኛው ምድብ ማየት እንደተሳናቸው ሁለተኛው ምድብ ደግሞ ማየት የሚችሉ ገፀባህሪያትን አስመስለው በመጫወት ማየት የማይችሉት አይናቸውን በሪቫን ጨርቅ ተሸፍነው እንዳይገልጡ ይደረጋል:: ማየት የሚችሉት ማየት የማይችሉትን በተወሰነ ርቀት ሆነው እንዲከተሉዋቸው በድምፅ ይመሩዋቸዋል::

በድምፅ የሚመሩትም አይናቸው የተሸፈኑትን ልጆች ከፊታቸው ካሉት ነገሮች ጋር እንዳይጋጩ እየጠበቁዋቸው በት/ቤቱ ግቢ የሆነ ሥፍራ እስኪደርሱ ያዙዋቸዋል:: ይህም ሲሆን አቅጣጫውን ለማመላከት ወደ ቀኝ ዙር/ሪ ወደ ግራ ዙር/ሪ ወደፊት ወደኋላ እያሉ በድምፅ ይረዱዋቸዋል እንጂ በእጅ አይነኩዋቸውም:: ይህን ተግባራዊ ክንዋኔ (ትዕዛዝ ለመስጠትና ለመቀበል) ወደ አሥር ደቂቃዎች ይስጡዋቸው:: ከዚያም «ማየት የማይችሉት» የአይን ሽፋን ሪቫን (ጨርቅ) በማስወለቅ በቦርሣ ወይም በሣጥን እንዲያስቀምጡ ማድረግ::

ለ. ከዚህ በኋላ ተማሪዎቹ ወደ ክፍል ሲመለሱ ማየት የተሳናቸውን ገፀባህሪ መስለው የተጫወቱትን ምን እንደተሰማቸው መጠየቅ:: ተመችቷችሁ ነበርን? ወይስ ከብዷችሁ ነበርን? የሆነው ሁሉ ግራ አጋብቷችሁ አለፈ? አይናችሁንስ ለመግለጥ ሙከራ አድርጋችሁ ነበርን? ወይስ በርግጥ መሃል ላይ ከፍታችሁ አይታችሁ ነበር? ይህስ ከሆነ ለምን አደረጋችሁ? በራሳችሁ መተማመን አቅቷችሁ ነበር ወይ? ይህን በመሰለ ሁኔታ ህይወትን ማሳለፍ ምን ይመስላችኋል? ጊዜ ከፈቀደ የቡድኖቹን ቦታ በመቀያየር ልምምዱን ደግሞ ማከናወን ይቻላል:: ይህ ሲሆን አዳዲስ የመሸፈኛ ሪባን መጠቀም የግድ ነው በተጨማሪም መምህሩ ይህን የመሰለ ልምምድ ከትምህርት ስዓት ውጪ እራሳቸውን በቡድን በመመደብ ያለ መሸፈኛ ሪባን እንዲሁ ዓይንን በመሸፈን (በመጨፈን) እንዲለማመዱ መምከር:: ይህም ከመምህራን እይታ ውጭ አንዱ በተሸፈነበት ሳይታጠብ ሌላው እንዳይጠቀምበት ለመከላከል ይረዳል ይህንኑ አስታውሶ መንገርም ያስፈልጋል::

## *አማራጭ ሁለት*

ሀ. ይህ ክንዋኔ ቁጥራቸው ከመጀመሪያ ባነሱ ጥቂት ተማሪዎች ሊከናወን የሚችል ሲሆን ከክፍል ሳይወጡ ጥቂት ተማሪዎችን በመምረጥ በሪባን አይናቸውን መሸፈን:: ከዚያም ማየት ለማይችሉ ተማሪዎች መምህሩ የተለያዩ ትዕዛዞችን በመስጠት የሚሆነውን መከታተል:: ለምሳሌ «ሂድና ከምሥጋናው አጠገብ ተቀመጥ» «ስምህን/ሽን ጥቁር ስሌዳው ላይ ፃፍ/ፊ» «የፋጡማን እርሳስ አንሣላት/ሽላት» ወዘተ... በሚገርም ሁኔታ እነዚህ ቀላል የሚመስሉ ትዕዛዞች «ማየት ለማይችሉት» ካለረዳት ማከናወን በጣም ከብዷቸው እናያለን:: እንደበፊቱ የተማሪዎችን አስተያየት መጠየቅና ማዳመጥ:: እንደከዚህ በፊቱ ከአንዴ በላይ የአይን መሸፈኛ ሪባኑን መጠቀም ለትራኮማ በሽታ መተላለፍያ መንገድ ስለሆነ አለመጠቀምን ማስገንዘብ ይገባል::

ከላይ በሁለቱ አማራጮች መጨረሻ መምህራን ተማሪዎችን ለምን የመሸፈኛ ሪባኑን ከአንድ ጊዜ በላይ እንዳይጠቀሙ እንደተከለከሉ ይጠይቁዋቸዋል:: ተማሪዎች የሰጡትን መልስ መምህራን ካዳመጡ በኋላ በማጠቃለል የመሸፈኛ ሪባኖቹ የጀርም መተላለፊያ እንዳይሆኑ ከአንድ ጊዜ በላይ መጠቀም እንደሌለባቸው ለተማሪዎቹ መንገርና ድጋሚም ለመጠቀም ከተፈለገ ከመጠቀማቸው በፊት ሪባኖቹ በሚገባ መታጠብ እንዳለባቸው ማስገንዘብ ያስፈልጋል::

**መምህሩ እዚህ ላይ ለምን ከአንዴ በላይ መጠቀም እንደሌለባቸው መደጋገም አይጠበቅበትም/ባትም:: ነገር ግን ይህንን መተላለፊያ መንገድ በተመለከተ ተማሪዎችን ማንቃት ያስፈልጋል።**

*የመምህሩ ማስታወሻ*

## 3. አነስተኛ የቡድን ሥራ: ዓይነስውራን በህብረተሰባችን ውስጥ

- የተሰጠው ጊዜ: 30 ደቂቃዎች
  የትምርት መርጃ: ማየት የተሳነው ሰው ምሥል
- አስፈላጊ ዝግጅት: ከማስተማርዎ በፊት ተግባራዊ ክንዋኔዎችን (activities) በሚገባ ያንብቡ

ሀ. መምህሩ የተማሪዎቹን ሙሉ ሀሳብ ለማግኘት ምስሉን በድጋሚ ለተማሪዎች በግልፅ ማሳየት:: ከዚያም ተማሪዎች ለ5 ደቂቃዎች በቡድን ተከፋፍለው በህብረተሰባቸው ውስጥ ያሉ ማየት የተሳናቸው ሰዎች በግላቸው መሥራት አይችሉም ብለው የሚያስቡትን እንዲናገሩ ማድረግና የእያንዳንዱን ተማሪ አስተያየት በጥቁር ሰሌዳ ላይ መፃፍ::

ማየት የተሳናቸው ሰዎች ብቻቸውን ሊፈፅሙ ከማይችሏቸው ነገሮች መካከል---------------- ይገኙበታል::

1. ወደ ቤተክርስቲያን መሄድ
2. ወደ ገበያ ቦታ መሄድ
3. ምግብ ማብሰል/እሳት መጠቀም
4. ለከብቶች መንገድ መልቀቅ
5. ማንበብ
6. ህፃናትን መንከባከብ

ከዚህ መልመጃ በመቀጠል ተማሪዎች ማየት በተሳናቸው ሰዎች ላይ ያለውን የህይወት ጫና በተጨባጭ እንዲረዱ ማድረግና የችግሩንም ባለቤቶች (ዓይነ ስውራንን) በቻሉት መንገድ እንዲረዱዋቸው ማሳሰብ (መንገር)::

ለ. - መምህሩ በጥቁር ሰሌዳ የተዘረዘሩ ነጥቦችን ለማከናወን ዘወትር የሌሎች እርዳታ ቢያስፈልጋቸው ኖሮ ምን ሊሰማቸው እንደሚችል ተማሪዎችን መጠየቅ፣

- ተማሪዎቹን የሚያስደስታቸው ጨዋታ ምን እንደሆነ መጠየቅ፣

* ከዚያም ማየት ቢሳናቸው ኖሮ እነዚህን አስደሳች ጨዋታዎች መጫወት ይችሉ እንደነበር መጠየቅ፣
* ተማሪዎቹ ምን አዘውትረው ማየት/መመልከት እንደሚወዱና እነዚያን ነገሮች ማየት ባይችሉ ምን እንደሚሰማቸው መጠየቅ፣

ለተማሪዎች ይህን ይንገሩዋቸው «የማየት ችሎታችን ለምን ለምን እንደሚጠቅመን አስቡና ይህንን ችሎታችንን ብናጣው ምን ያህል ህይወታችን እንደሚከብድም አስተውሉ፤ ይህም ሲባል በጣሙን የከፋ ችግር ልናስበው ከምንችለው በላይ የሆነ»

ሐ. መምህር ተማሪዎችዎ የትምህርቱን ቁልፍ ሀሳብ «ዓይኔ እጅግ በጣም ያስፈልገኛል» «ማየት መቻል በጣም ያስፈልገኛል» የሚለውን በማስታወሻ ደብተራቸው እንዲፅፉት ያድርጉ::

መ. መምህሩ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከተቻለ በወረቀት አባዝቶ ካልተቻለም በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ እንዲያሟሉት ያድርጉ::

ማየት ባልችል ኖሮ ------------------ ማድረግ አልችልም ነበር::
ማየት ባልችል ኖሮ ------------------- ማድረግ ይኖርብኝ ነበር::
ማየት ባልችል ኖሮ ------------------- ማየት አልችልም ነበር::
ማየት ባልችል ኖሮ ------------------- በጣም ይናፍቀኝ ነበር::
ማየት ባልችል ኖሮ -------------- ይሰማኝ ነበር::
ማየቴ ለእኔ ጥቅም አለው ምክንያቱም ----------------------::

***የመምህሩ ማስታወሻ***

## 4. በህብረተሰቡ ውስጥ ካሉ ዓይነስውራን ጋር ቃለ ምልልስ በማድረግ መሟላት ያለባቸው ነገሮች::

የተሰጠው ጊዜ: እስከ 20 ደቂቃዎች (ይህ በምዕራፍ ሁለት ይደገማል)
የትምህርት መረጃ: ምንም አያስፈልግም

አስፈላጊ ዝግጅት፡ ከማስተማርዎ በፊት ተግባራዊ ክንዋኔዎች (activities) በሚገባ ያንብቡ፡፡

ሀ. መምህሩ ተማሪዎች ስለ ዓይነ ስውራን ሰዎች በጥልቀት ለመረዳት እንዲችሉ ለዓይነ ስውራን ግለሰቦች ቃለመጠይቅ ማድረግ ተመራጭና አስተማማኝ ዘዴ መሆኑን ማስረዳትና በቤት ሥራ መልክ ጠይቀው እንዲመጡ ከዚህ በታች ያሉትን ጥያቄዎች እንደምሳሌ መስጠት፡-

- መቼ ነው ዓይነ ስውር የሆንከው/ሽው?
- ላንተ/ቺ ዓይነ ስውር መሆን ማለት ምን ማለት ነው? ምንስ ተሰማህ/ሽ?
- ዓይነ ስውር ከሆንክ በኋላ በህይወትህ/ሽ የሆነው ለውጥ እንዴት ነበር?

**አስተውሎት**፡ እነዚህ ጥያቄዎች ከተወለደ ጀምሮ ዓይነ ስውር የሆነን ሰው አይመለከትም፡፡

ለ. ተማሪዎች የተነሱትን ጥያቄዎች በማስታወሻ ደብተራቸው እንዲፅፉዋቸው ከተነገራቸው በኋላ የተዘረዘሩትን ጥያቄዎች እንዴት ተጠያቂዎቻቸውን እንደሚጠይቁ መምህራን ያስረዱዋቸዋል፡፡ ከዚያም ከ------------ ቀናት በኋላ የቤት ሥራውን ማስረከብ እንዳለባቸው ይነግሩዋቸውና አራት ወይም አምስት ተማሪዎች ያሉበት ቡድን ይመደባሉ፡፡ (አመዳደቡ እንደቤታቸው ቅርበት ቢወሰን ነገሮችን ከማቅለሉም ባሻገር ብልህነት ነው ምክንያቱም ከትምህርት ቤት ውጪ በቀላሉ ተገናኝተው ሊሠሩ ይችላሉና)፡፡ በእያንዳንዱ ቡድን ውስጥ አንዱ እንኳን የሚያውቀውና ሊጠይቁት የሚችሉት ዓይነስውር ሰው ስለመኖሩም ያረጋግጡ፡፡ በመጨረሻም ተማሪዎቹ ቃለ መጠይቁን ቃል በቃል ከመመዝገብ ይልቅ በጣም ጠቃሚ የሆኑ ሀሳቦችን ብቻ እንዲያሰፍሩ መንገር፡፡ እነዚህ ነጥቦችም በቀጣዩ የትምህርት ክፍለ ጊዜ መወያያ ነጥቦች እንዲሆኑ ማድረግ፡፡ ይህ መሆን ካልቻለ ግን መምህሩ አንድ በጎፈቃድ ያለው ማየት የተሳነው ሰው ወደ ክፍሉ በመጋበዝ ተማሪዎቹ ጥያቄዎችን እንዲጠይቁት ማድረግ እንደ ሌላ አማራጭ መያዝ ይኖርበታል፡፡

ሐ. በቀጣዩ ክፍለ ጊዜ ወይንም መምህሩ በወሰነው ሰዓት ተማሪዎች በሰበሰቡዋቸው ቃለ ምልልሶች ላይ ለመወያየት ተዘጋጅተው እንዲመጡ ተደርጎ መምህሩ የመጡት ነጥቦች ከዚህ ቀደም በክፍል ውስጥ ስለ ዓይነ ስውር ሰዎች ከተነሱ ነጥቦች ጋር እያጣቀሱ ማጠቃለያ የሆነ ሀሳብ ይሰጡበታል፡፡

*የመምህሩ ማስታወሻ*

## 5. የዓይን የተለያዩ ክፍሎች

የተሰጠው ጊዜ: 30 ደቂቃ

የትምህርት መረጃ: የዓይን ምሥል

አስፈላጊ ዝግጅት: ተግባራዊ ክንዋኔዎችን (activities) በድጋሚ ማንበብና የዓይን ክፍሎች የሚያሳየውን ስዕል ማጥናት

ሀ. መምህሩ ተማሪዎች በጥንድ (ከጓደኛ ጋር) የአይን ሥዕል እንዲሠሩ ማድረግና በየተራ አንዱ የሌላኛውን ዓይን የደብተሩን ግማሽ ገጽ በመጠቀም እንዲስል ማድረግ:: ምን ያህሉን የዓይን ክፍሎች አስተውለዋል? መምህሩ የዓይንን ልዩ ልዩ ክፍል የሚያሳይ ምሥል በእጅዎ ከሌለ ተማሪዎቹ ሥራውን እስኪጨርሱ ድረስ እርስዎም በጥቁር ሰሌዳው ላይ መሳል ይኖርብዎታል። ተማሪዎቹ ስዕሉን ከጨረሱ በኋላ የዓይን የተለያዩ ክፍል ስሞች ሊፅፉ እንደሚችሉና እንደማይችሉ መጠየቅ:: የእያንዳንዱ ክፍል ተግባር ምንድነው? ብሎ መጠየቅ ከዚያም እያንዳንዱን የዓይን ክፍል ማስረዳት:: ከዚያም የሳሉት ስዕል ላይ በሚገባ እንዲያስፍሩ ማድረግ:: በመጨረሻም ተማሪዎቹ የአይንን የጎንዮሽ ገፅታ ከምሥሉ ላይ በደብተራቸው እንዲሥሉ ማድረግ::

ለ. መምህሩ ከዚህ ልምድ በኋላ ምሥሉን ይዘውት ባይሄዱ ይመረጣል:: ምክንያቱም ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ሥዕሉን በማየት የበለጠ እንዲረዱ ይረዳቸዋልና:: ይህ ተሞክሮ አጥጋቢ መሆኑ በኔፓል በተካሄደ የመማር ማስተማር ልምድ ልውውጥ ስብሰባ ላይ ተገልጿል::

*የመምህሩ ማስታወሻ*

## የዓይንን የተለያዩ ክፍሎች መረዳት

የትምህርት መርጃዎች


- ነጭ ወረቀት
- እስክሪብቶ/እርሳስ
- ቻርት (chart) የዓይንን የፊትና የጎንዩሽ ገፅታ የሚያሳዩ ሁለት ትላልቅ ተጠቅላይ ምሥሎች
- ማስታወሻ (handout) የዓይንን ምሥል የያዘ ነገር ግን የክፍሎቹ ሥያሜ ያልተፃፈበት ለተማሪዎች የሚታደል ወረቀት


ዓላማው፡ የዓይንን የተለያዩ ክፍሎችና ሥራዎቻቸውን መግለፅ ይችላሉ::

## የአቀራረብ ቅደም ተከተል


- በክፍል ውስጥ ለሚገኙት ተሳታፊዎች በሙሉ ንፁህ ወረቀትና እርሳስ በመስጠት ጓደኛ ከመረጡ በኋላ የጓደኞቻቸውን አንድ ዓይን እንዲሥሉ ማድረግና ምን ያህሉን የዓይን ክፍሎች ሊያመለክቱ እንደቻሉ መጠየቅ::
- የዓይንን የፊት ለፊት ገፅታ የያዘውን ምሥል በማሳየት የሚያውቋቸውን የተለያዩ ክፍሎች ስያሜ መጠየቅና በሥዕላቸውም ላይ እንዲያሳዩት ማድረግ:: ስለሚያውቁት የዓይን ክፍል በበለጠ እንዲያብራሩ ማበረታታትና መምህሩም ሁሉንም የአይን ክፍሎችና በተለይም ተማሪዎች ሊጠቅሷቸው ያልቻሏቸውን ማስረዳት ይኖርባቸዋል:: በመቀጠል የጎንዮሽ ገፅታ የያዘውን ምሥል በማሳየት የተለያዩ የዓይን ክፍሎችን በድጋሚ ማስረዳት::


# ኣባላተ ስሜት እይታ
## sense organs : sight



## አባላተ ስሜት እይት
## sense organs : sight





## ክፍለ ትምህርት ሁለት

# የትራኮማ በሽታ ምንድነው? እንዴት ይተላለፋል? ዓይነ ስውርነትን እንዴት መከላከል ይቻላል?

### ቁልፍ መልዕክቶች

- «አክቲቭ ትራኮማ የላይኛው ዓይነ ቆብ ወደ ውስጥ መቀልበስን ወይም ዓይነ-ፀጉር (ትሪኪያሲስ) ሊያስከትል ይችላል»
- «በትራኮማ የሚመጣ ዓይነ ስውርነትን እንዴት መከላከል ይቻላል? በ(ማ[1]መ[1]ን[2])» መርሆች
- «ማየት በጣም ስለሚያስፈልገን ትራኮማን በ «ማመን» ሥልት መግታት አለብን»

## የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች

1. ተማሪዎች በትራኮማ ሕመም (active trachoma)፣ በዓይን ቆብ መቀልበስ ወይም ዓይነ-ፀጉር (trichiasis) እና በዓይነ ስውርነት (blindness) መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት (ሦስቱም የአንድ በሽታ የተለያዩ ደረጃዎች መሆናቸውን) ይገነዘባሉ።
2. ተማሪዎች የትራኮማ ሕመም (active trachoma) ምልክቶችን በትክክል ይዘረዝራሉ (ይተነትናሉ)።
3. ተማሪዎች የዓይን ቆብ መቀልበስን ወይም ዓይነ ፀጉር (trichiasis) የተለያዩ ምልክቶች ይለያሉ።
4. ተማሪዎች የትራኮማ በሽታ ዋና ዋና መተላለፊያ መንገዶችን ይዘረዝራሉ (ከሰው ወደሰው፣ መሐረቦችን በጋራ በመጠቀምና በዝንቦች)።
5. ተማሪዎች በትራኮማ በሽታ የሚመጣን ዓይነ ስውርነት እንዴት መከላከል እንደሚቻል በሚገባ ይተነትናሉ።

## ተግባራዊ ክንዋኔዎች

1. ክላሣ (ለ 15 ደቂቃ)
2. አዲስ መጽሐፍ ስለትራኮማ የሚተርከውን ማንበብ (ለ 30 ደቂቃ)
3. የአዲሱን መጽሐፍ ሀሳብ በተጠናከረ መልክ ማቅረብና የ(«ማመን») ተግባር ማስተዋወቅ (ከ 15-20 ደቂቃ)

4. ስዕል መሳል (30 ደቂቃ)
5. ስለ «ማመን» ተግባር የሚገልፅ መዝሙር አዘጋጅቶ ማዘመር (በተጨማሪ ጊዜ)
6. በድራማ መልክ መከለስ (60 ደቂቃ)
7. ተዘበራርቀው የተቀመጡ ዐረፍተ ነገሮችን በሀሳብ ቅደም ተከተል እንዲያስይዙ በማድረግ መከለስ (15 ደቂቃ)
8. በእውነት/ ሀሰት መልክ ጥያቄዎችን እንዲመልሱ በማድረግ ሀሳቦችን መከለስ (15 ደቂቃ)
9. በቃል የሚመለሱ ጥያቄዎችን በመጠየቅና በመመለስ መከለስ (5 ደቂቃ)

ይህን ክፍለትምህርት ለመጨረስ በግምት ወደ አምስት ሰዓት ይፈጃል፡፡

**1. "የአይኔ ብርሃን እጅግ ያስፈልገኛል"**

**ክለሣ**: "ማየት መቻሌ በጣም ያስፈልገኛል

**የተሰጠው ጊዜ**: እስከ 60 ደቂቃ

**የትምህርት መርጃ**: መሣሪያዎች

**ቅድመ ዝግጅት**: ከማስተማርዎ በፊት የተግባራዊ ክንዋኔዎችን በሚገባ ማንበብ፡፡ ተማሪዎቹን እንደአስፈላጊነቱ የሚያውቁትን ታሪክ የሰሙትን ቃል ምልልስ ለክፍል ተማሪዎች እንዲያቀርቡ መጋበዝ፡፡

## *አማራጭ አንድ*

ከዚህ በፊት በክፍለ ትምህርት አንድ ተግባራዊ ክንዋኔ 4 ላይ ያልተከናወነ ከሆነ ብቻ በቃለ መጠይቁ ወቅት የተነሱ ጥያቄዎችን በየተራው በማንሣት ተማሪዎቹ ማንን እንደጠየቁና እንዳነጋገሩ፣ ከቃለመጠይቁ ምን እንደተማሩ ለክፍሉ ተማሪዎች እንዲያካፍሉ ማድረግ

## *አማራጭ ሁለት*

ተማሪዎችን ተራ በተራ በማስነሳት ያመጡትን ታሪክ ለክፍሉ በሙሉ አለበለዚያም በቡድን ሆነው እንዲያነቡት ማድረግ (በአንድ ክፍል ውስጥ ጥቂት ተማሪዎች ካነበቡ ይበቃል)፡፡ ይህ የሚሆነው የዚህ ዓይነት የመማር ማስተማር ሂደት ካልተካሄደ ብቻ ይሆናል፡፡

## *አማራጭ ሦስት*

በተለያዩ ምክንያቶች ተማሪዎቹ ቃለ ምልልሱን ካላደረጉ መምህሩ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ምሳሌዎች መሠረት በጎደለ ቦታ መሙላት መልመጃ ይሰጣቸው:: ለምሳሌ ጥቁር ሠሌዳው ላይ «ማየት መቻሌ ለኔ በጣም የሚያስፈልግበት ምክንያት -------------------------» የሚለውን ጥያቄ መፃፍ:: ቀጥሎም ከዚህ በፊት የተወያዩባቸውን ነጥቦች እንዲያስታውሱ ማድረግ፤ በዚህም መሠረት ፈቃደኛ ተማሪዎች ጥያቄውን በቃል እንዲመልሱ ማድረግ፣ ግዜ ከፈቀደ እንዲፅፉት ቢደረግ የበለጠ ጥሩ ይሆናል::

**ለምሳሌ:-**

«ማየት መቻሌ በጣም የሚያስፈልገኝ---- ማንበብ ስለሚረዳኝ ነው::»

«--- ተደናቅፌ እንዳልወድቅ ስለሚጠቅመኝ ነው::»

«የተለያዩ ጨዋታዎችን በቀላሉ ለመጫወት ስለሚያስችለኝ ነው::»

## *የመምህሩ ማስታወሻ*

## 2. አዲስ የትምህርት መርጃ መሣሪያ ማስተዋወቅ

ስለ ትራኮማ የሚተርክ መጽሐፍ

የተሰጠው ጊዜ: 30 ደቂቃ

የትምህርት መርጃ መሣሪያ: መጽሐፍ/ ስለትራኮማ

ቅድመ ዝግጅት: ከማስተማርዎ በፊት የተግባራዊ ክንዋኔዎችን በሚገባ ማንበብ:: ይህን የመሰለ መጽሐፍ ተማሪዎች አንብበው የማያውቁ በብዛት ሊኖሩ ስለሚችሉ ንባቡ በዝግታ መሆን ይኖርበታል:: ምክንያቱም ተማሪዎቹ የምንባቡን ሙሉ መልዕክት በሚገባ እንዲረዱት ይፈለጋልና::

**አቀራረብ:-**

1. መምህሩ ለክፍሉ ተማሪዎች የሚከተለውን መንገር «ከዚህ ቀደም ዓይነ ስውርነት ምን ሊመስል እንደሚችልና ማየት መቻላችን እንዴት እንደሚጠቅመን በሰፊው አይተናል:: ዛሬ ደግሞ ስለ አንዲት ዓይነ ስውር ሴት እንዴት የዓይንዋን ብርሃን እንዳጣች የሚተርክ ምንባብ አነባላችኋለሁ:: ታሪኩን በማነብላችሁ ወቅት ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከምትሰሙት ምንባብ መልስ እንደምትፈልጉላቸው አትዘንጉ:: ምንባቡን ሰምታችሁ ሳትጨርሱ መልሱን መፃፍ የለባችሁም::«ምንባቡን ስጨርስ አብረን እንሠራዋለን:: »

## እነዚህ ጥያቄዎች ለህፃናት ተማሪዎች ይመጥናሉ

1.1. አሮጊቷ ህፃን ሣለች ማድረግ የጠላችውና በትራኮማ በሽታ በቀላሉ እንድትጠቃ ምክንያት የሆናት ምንድነው?

1.2. የትራኮማ ሕመም ( active trachoma) ምልክቶች ምንድናቸው?

1.3. ትራኮማን ለሚያስከትል ጀርም እንዴት እንጋለጣለን?

1.4. አንድ ሰው በትራኮማ በሽታ በተደጋጋሚ መያዙ ምን ሊያስከትልበት ይችላል?

1.5. የዓይን ቆብ መቀልበስ ወይም ዓይነ-ፀጉር (trichiasis) በሽታ ምልክቶች ምንድን ናቸው?

1.6. ትራኮማ፣ የዓይን ቆብ መቀልበስ ወይም ዓይነ-ፀጉር (trichiasis) እና ዓ ይነ ስውርነት (blindness) ግንኙነት አላቸውን?

1.7. ህፃናት በትራኮማ ሊመጣ የሚችለውን ዓይነ ስውርነት (የዓይን ጉዳትን) እንዴት መከላከል ይችላሉ? (በእድሜ ከፍ ላሉት ደግሞ ይህን የመሠለ ከበድ የሚል ጥያቄ ማቅረብ ይቻላል)

1.8. ህፃናት ስለ ዓይነ-ፀጉር (trichiasis) የሚጠነቀቁና የሚያስቡ ይመስልሃል/ሻል ወይስ ይህ ችግር የሚመለከተው አዋቂዎችን ብቻ ነው?

2. መምህሩ ስለትራኮማ የተፃፈውን መጽሐፍ ሁሉም የክፍሉ ተማሪዎች በሚያዩበት ሥፍራ እንዲቀመጥ ማድረግ:: ይህም ሁሉም እንዲያነቡት ያስችላል:: በገጽ 6 መጨረሻ ላይ እያዩ አያቱን «እኔስ ትራኮማን እንዴት መከላከል እችላለሁ?» ብሎ ሲጠይቅ መምህር ማንበብዎን አቋርጠው የአያትየው መልስ ምን ሊሆን እንደሚችል ተማሪዎቹን ማስሞከር:: የሰጡትን መልስ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ በሚቀጥለው ገጽ ላይ ያገኙታል::

3. ምንባቡ እንደተጠናቀቀ ተማሪዎች ለተጠየቁት ጥያቄዎች መልሶችን በቃል እንዲሰጡ ማድረግ:: (መልሶቹን ከታች ይመልከቱ) ይህም ሲሆን እርማት በሚያስፈልግበት ቦታ ላይ ተገቢውን እርማት መስጠት ይገባል:: መልመጃው ለተማሪዎቹ ከከበደ መምህር ድምፁን ከፍ በማድረግ ምንባቡን በድጋሚ መተረክ ይቻላል:: በዚህ ወቅት ለተነሡት ጥያቄዎች መልስ የሚሆኑ ነጥቦች ላይ ጥያቄዎችን በድጋሚ መጠየቅ:: ተማሪዎች ትክክለኛውን መልስ ማወቃቸውን ማረጋገጥ:: በማስታወሻ ደብተራቸውም እንዲጽፉት ማድረግ::

3.1. አሮጊቷ ህፃን ሳለች ማድረግ የማትወደውና ለትራኮማ በሽታ በቀላሉ መያዝ ምክንያት የሆነባት ምንድን ነው?

- በፍፁም ፊትዋንም ሆነ እጆችዋን መታጠብ መጥላትዋና ዘወትር ቆሻሻ መሆኗ::

3.2. የትራኮማ (active trachoma) በሽታ ምልክቶች ምንድናቸው?

- አይንን መለብለብ፣ ማሳከክና ማሞጭሞጭ እንዲሁም አንዳንዴ የንፍጥ መብዛት ማስከተል::

3.3. ለትራኮማ (active trachoma) በሽታ ጀርሞች እንዴት እንጋለጣለን? በሰዎች (በአዋቂም ሆነ በህፃናት) መካከል በሚደረግ ንክኪና ዝንቦች ከቆሻሻ ቦታ ተነስተው በአይናችን አካባቢ ሲያርፉ ለጀርሞቹ እንጋለጣለን::

3.4. ሰዎች በተደጋጋሚ ትራኮማ ከታየባቸው ምን ሊያስከትል ይችላል?

- የትሪኪያሲስ የአይን መቅላትና ማሳከክ ሊያስክትል ይችላል

3.5. የትሪኪያሲስ በሽታ ምልክቶች ምንድናቸው?

- የዓይነ-ፀጉር (trichiasis) በሽታ ምልክቶች የላይኛው የዓይን ቆብ ወደ ዓይናችን ውስጥ መታጠፍና መለብለብ

3.6. ትራኮማ (active trachoma) ፣ ዓይነ-ፀጉር (trichiasis) እና ዓይነ ስውርነት (blindness) በሽታዎች የተያያዙ ናቸውን?

- አዎን ሦስቱም የአንድ በሽታ የተለያዩ ደረጃዎች ናቸው::

3.7. ህፃናት የትራኮማ በሽታ የሚያስከትለውን ዓይነ ስውርነት እንዴት መከላከል ይችላሉ?

- ህፃናት ዘወትር በቆሸሹ ግዜ ሣይታክቱ እጃቸውንና ፊታቸውን ቢታጠቡ (ቢያንስ በቀን ሁለት ጊዜ)፣ መሐረቦቻቸውን ለሌሎች ባለመስጠት፣ የትራኮማ በሽታ ስሜቶች ሲኖርባቸው ለቤተሰቦቻቸውና ለመምህሮቻቸው ወይም ለጤና ባለሙያዎች ወዲያውኑ በመንገር (teteracycline) የዓይን ጠብታ ሣያቆርጡ በመውሰድ፣ እንዲሁም ለሌሎች ልጆች ፊታቸውን

እንዲታጠቡና የዓይነ ምድርን በሽንት ቤት እንዲጠቀሙ በመንገር ሊከላከሉ ይችላሉ።

**በእድሜ ከፍ ላሉ የሚቀርብ ከበድ ያለ ጥያቄ**

**3.8. ህፃናት ስለ ዓይነ-ፀጉር (trichiasis) የሚጨነቁ ይመስልሃል/ሻል ወይስ ይህ ችግር የሚመለከተው አዋቂዎችን ብቻ ነው?**

- ህፃናት ስለ ዓይነ ፀጉር (trichiasis) መጨነቅና ማሰብ አለባቸው። ምክንያቱም በሽታው በህፃንነት ጊዜ በተደጋጋሚ የሚከሰት ነውና። ህፃናት በዚህ ዕድሜያቸው ይህንን ተረድተው ንፅህናቸውን ካልጠበቁ ወደፊት በበሽታው ሊጠቁ ይችላሉ።

## *የመምህሩ ማስታወሻ*

3. የ ማመን መርሆዎች

(ማስቀረጥ (በቀዶ ሕክምና ): መድሃኒት፣ የፊት ንፅህና እና የአካባቢ ንፅህና)

ስለበሽታው በአዲስ መልክ የተጠናከረ ግንዛቤን ማስጨበጥ

የተሰጠው ጊዜ: ከ 15-20 ደቂቃ

የትምህርት መርጃ መሣሪያ: ስለትራኮማ የሚተርክ መጽሐፍና ወደ ዓይነ ስውርነት የሚያመራ የትራኮማ ቁልቁለት ፖስተር

ቅድመ ዝግጅት: ከማስተማርዎ በፊት የአክቲቪቲዎችን ትረካ መጽሐፍ ማንበብ።

1. የትራኮማን በሽታ ሂደት የሚያሳየው ሥዕል ፣

(በህብረተሰብ ተሳትፎ የዓይን ማዝ በሽታን መቆጣጠር በሚለው መጽሐፍ ገፅ 3 ይመልከቱ) ትራኮማ (trachoma) ፣ ዓይነ-ፀጉር (trichiasis) እና ዓይነ ስውርነት (blindness) የአንድ በሽታ የተለያዩ እርከኖች መሆናቸውን በድጋሚ ማስረዳት፣ ጊዜ ከፈቀደም መምህር ሥዕሎቹን እያጣቀሱ ተማሪዎች በቃል የሚመልሱዋቸውን ጥያቄዎች መጠየቅ:: ይህም ከዚህ በፊት ተማሪዎች የተማሩትን ለማስታወስ ብሎም የበሽታውን መንስኤና የሚያስከትለውን አደጋ እንዲሁም በትራኮማና በዓይነ ስውርነት መካከል ያለውን ግንኙነት በደንብ እንዲያስተውሉ ይረዳል::

**ለምሳሌ:-**

መምህር የትራኮማ ዕድገት የሚያሣየውን ምስል/ፖስተር (ከላይ ከተጠቀሰው መጽሐፍ ገፅ 3) ማየት ከተሳነው በመጀመር ወደኋላ እየጠቆሙ ካሣዩ በኋላ እነዚህን ጥያቄዎች ይጠይቁ::

«እነዚህ ሰዎች ማየት ይችላሉን? ስለነዚህ ሰዎች ንገሩኝ::»

ተማሪዎቹ ሰዎቹ ማየት የማይችሉ አዛውንቶች ናቸው ብለው መመለስ አለባቸው::

«ለምንስ ታወሩ?»

የአይን ፀጉር ወደ ውስጥ መቀልበስ ወይም ዓይነ-ፀጉር ትሪኪያሲስ (trichiasis) የዓይን ብርሃን በሽፍሽፋቶች መፋቅ፣

«ግን ለምን ዓይነ-ፀጉር (trichiasis) ያዛቸው?»

ምክንያቱም ዓይናቸውን በትራኮማ በተደጋጋሚ ስለተጠቁ ነው::

«ለምን አክቲቭ (active) ትራኮማ ያዛቸው?»

ምክንያቱም ፊታቸውን ስለማይታጠቡ (ቆሻሻ ስለነበር) እና በሽታውም ተላላፊ ስለሆነ በአይኖቻቸው ላይ የሚያርፉት ዝንቦች በቀላሉ ጀርሞቹን ከአንዱ ወደ ሌላው በማባዛታቸው ነው::

እንደ አማራጭ በዕድሜ ከፍ የሚሉትን ተማሪዎች በማስነሳት ስለበሽታው እድገት ሥዕሉን እያጣቀሱ እንዲገልጹ ማድረግ ይቻላል::

2. መምህር ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መልዕክቶች በጥቁር ሰሌዳው ላይ በመፃፍ ተማሪዎቹ እንዲገለብጡት ያድርጉ
   - ተከታታይ ትራኮማ ወደ ዓይነ-ፀጉር (trichiasis ) ሊሸጋገር ይችላል::
   - በትራኮማ አማካኝነት የሚመጣን ዓይነ ስውርነትን እንዴት መከላከል ይቻላል? **ማመን** (SAFE)
   - ዓይናችን በጣም ስለማያስፈልገን ትራኮማን መከላከል አማራጭ የሌላው ዘዴ ነው:: **ማመን** (SAFE)

## የመምህሩ ማስታወሻ

3. ስዕል መሣል
የተሰጠው ጊዜ:-    30 ደቂቃ
የትምህርት መርጃ መሣሪያ:- ለተማሪዎች ስዕል መሳያ ሰፊ ወረቀትና እርሳስ
ቅድመ ዝግጅት:- ከማስተማርዎ በፊት ተግባራዊ ክንዋኔዎችን ( activities ) በሚገባ ያንብቡ

3.1. መምህር ተማሪዎች የትራኮማ በሽታን ሂደት ወደ ዓይነ ስውርነት ማምራቱን የሚያሳየውን ቁልቁለት ፖስተር እንዲሠሩ ያበረታቱ፡፡ ዋናውን ሞዴል እንዲያስተያዩ ከፊት ለፊታቸው አስቀምጠው የራሳቸውን ፈጠራ በመጠቀም እንዲሠሩ በክፍል ውስጥ እየተዟዟሩ ይመልከቱ፡፡

## የመምህሩ ማስታወሻ

4. በመዝሙር መልክ የ "ማመን" መንገዶች ማቅረብ
የተሰጠው ጊዜ: በትርፍ ጊዜ የሚከናወን
የትምህርት መርጃ መሣሪያ: ምንም አያስፈልግም
ቅድመዝግጅት: ከማስተማርዎ በፊት ተግባራዊ ክንዋኔዎችን /Activities/ በሚገባ ያንብቡ

መዝሙሮች በቀላሉ መልዕክት የማስተላለፍ ብቃት አላቸው፡፡ በቁጥር ከ 5 እስከ 7 ያሉ ተማሪዎች በቡድን በመመደብ ሌሎችን ሊረብሹ በማይችሉበት ሁኔታ ለጥቂት ቀናት መዝሙሮች እንዲያዘጋጁና እንዲያጠኑት ያድርጉ፡፡ ከዚህ በኋላ ተማሪዎች

ካቀረቧቸው መዝሙሮች ውስጥ ተመራጭ የሆነውን መዝሙር በትምህርት ቤቱ የሰንደቅ ዓላማ ሥነ ስርዓተ እንዲቀርብ ያድርጉ ከዚህ በተጨማሪ ተማሪዎች መዝሙሮችን ከትምህርት ቤት ውጪም እንዲዘምሩ ያበረታቱ::

***የመምህሩ ማስታወሻ***

## 5. በድራማ መልክ ትምህርቱን መከለስ

**የተሰጠው ጊዜ:** 60 ደቂቃ

**የትምህርት መርጃ:** ስለ ትራኮማ በሽታ የሚተርክ መጽሐፍ

**አስፈላጊ ዝግጅት:** መምህር ከማስተማርዎ በፊት ተግባራዊ ክንዋኔዎችን /Activities/ በሚገባ ያንብቡ

5.1. መምህር ስለ ትራኮማ የተፃፉትን የተለያዩ ታሪኮች ከተማሪዎች ጋር በመሆን ይወያዩ:: ከነዚህም አንዱ ስለ እያዩና ስለ አያቱ የተፃፈውን ታሪክ በድራማ እንዲተውኑት ማድረግ ነው:: ከታሪኩ ጋር የሚጣጣም ድርሰት በመጨመር መተወን ይቻላል:: ሆኖም ተማሪዎቹ የመጽሐፉን መልዕክት በሚገባ ማስተዋልና የተሰጣቸውን ገፀ-ባህሪ አጥንተው ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል:: ለድራማው ዝግጅት ክፍሉ በቂ ከሆነ ብዙ ተማሪዎች ማቅረብ ይችላሉ:: ከዚህ ባሻገር ተማሪዎች ሌላ ቦታ ማቅረብ እንደሚችሉ መጠየቅና ቢያንስ አንድ ጊዜና አንድ ቦታ እንዲያቀርቡት ማመቻቸት:: ይህም በቤታቸው አካባቢ በሚጫወቱበት ሥፍራ፣ በትምህርት ቤት፣ በቤተክርስቲያን ወይም በጤና ጣቢያዎች፣ ሊሆን ይችላል:: ከዚህም በኋላ የተማሪዎችን ፕሮግራም ማወቅና ከሰሩም በኋላ በወቅቱ የገጠማቸውን የተመልካቾች አመለካከት ጥያቄዎች ቀርበውላቸው እንደነበረና በአብዛኛው ተመልካቾች የነበሩት እነማን እንደሆኑ ወዘተ ይወያዩ::

***የመምህሩ ማስታወሻ***

**6. ዐረፍተ ነገሮችን በቅደም ተከተል የማስቀመጥ ክለሣ**
**የተሰጠው ጊዜ፡** 15 ደቂቃ
**የትምህርት መርጃ፡** ምንም አያስፈልግም
**አስፈላጊ ዝግጅት፡** መምህር ከማስተማርዎ በፊት ተግባራዊ ክንዋኔዎችን /Activities/ ያንብቡ

6.1. በትራኮማ **(active trachoma)** ፣ በዓይነ-ፀጉር (trichiasis) እንዲሁም በዓይነ ስውርነት (blindness) መካከል ያሉትን ግንኙነቶች መከለስ:: መምህር ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን አምስት ዐረፍተ ነገሮች በጥቁር ሠሌዳው ላይ ከፃፉ በኋላ ተማሪዎቹ በደብተራቸው ላይ በትክክለኛው ቅደም ተከተል እንዲያሰፍሩ ይንገሩዋቸው:: በመቀጠልም የክፍል ተማሪውን ሥራ በህብረት ማረም:: ይህም ዐረፍተ ነገሮቹ ቀለል ብለው እንዲታዩ ለማድረግ ያስችላል::

- ዓይነ-ፀጉር ስለያዛት የዓይኖቿ ሽፋሽፍቶች ከአይኖቿ ጋር ጠብ ያላቸው ይመስላሉ /4/
- ዓይኖችዋን ብዙ ጊዜ ታካለች፣ እንባም አይለያቸውም ነበር:: ይህም ዝንቦች ከፊቷ ላይ እንዳይጠፉ ምክንያት ሆኗል:: ያለ ጥርጥር በትራኮማ ሕመም ተይዛለች:: /2/
- ከሁሉም የሚያሳዝነው ደግሞ የዓይነ-ፀጉሩ ስታድግ ዓይነ ስውር ስላደረጋት ነው/5/
- ከብዙ ዓመታት ህመም በኋላ የአይኖቿ ሽፋሽፍቶች የውስጠኛው ክፍል የማይጠፉ ጠባሳዎች አስቀረ ይህ ደግሞ ወደ ውስጥ እንዲቀለብሱዋቸው አድርጓል:: /3/
- አያቴ ትንሽ ልጅ እያለች ፊትዋን አትታጠብም ነበር:: /1/

## *የመምህሩ ማስታወሻ*

## 7. ክለሣ በእውነት / ሀሰት ጥያቄዎች

**የተሰጠው ጊዜ:** እስከ 15 ደቂቃ

**የትምህርት መርጃ:** ምንም አያስፈልግም

**አስፈላጊ ዝግጅት:** መምህር ከማስተማርዎ በፊት ተግባራዊ ክንዋኔዎች /Activities/ በሚገባ ያንብቡ

7.1. በአክቲቭ ትራኮማ፣ በዓይነ-ፀጉር እና በዓይነ ስውርነት መካከል ያለውን ግንኙነቶች በእውነት /ሐሰት ዐረፍተ ነገሮች እየጠየቁና እየመለሱ መከለስ:: እባክዎ መምህር ይህን በቃልዎ ያድርጉ ተማሪዎችም መልሱን በቃል ይስጥዎት:: ነገር ግን ተማሪዎችዎ ለመፃፍ ከፈለጉ በዝግታ እስኪጽፉ በመጠበቅ በሙከራ ጥያቄ መልክ ክፍል ውስጥ እንዲሰሩ አድርገው መልሱን ይንገሩዋቸው ወይንም ተማሪዎቹ የየራሳቸውን እውነት /ሐሰት ጥያቄዎች በማውጣት ክፍል ውስጥ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር ይጠያየቁ። ወይንም ክፍሉን በሁለት በመከፈል ሁለቱም ምድብ አንዱ ከሌላኛው የእውነት/ሐሰት ጥያቄዎችን በማቅረብ እርስ በርሳቸው በየተራ ውጤት እየመዘገቡ እንዲፈታተኑ ማድረግ እንደ ዕድሜያቸው ክልል ተገቢው ጥያቄ በግልጽ መቅረቡንም ማረጋገጥ::

***የመምህሩ ማስታወሻ***

**8. በቃል ጥያቄዎች መከለስ**
**የተሰጠው ጊዜ: 5 ደቂቃ**
**የትምህርት መርጃ: ምንም አያስፈልግም**
**አስፈላጊ ዝግጅት: መምህር ከማስተማርዎ በፊት ተግባራዊ ክንዋኔዎችን /Activities/ በሚገባ ያንብቡ**

8.1. ተማሪዎችን የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይጠይቁ

«ዓይነ ስውርነትን መከላከል ይቻላልን? ዓይነ-ፀጉርንስ (trichiasis) ማቆም እንችላለን? «ትራኮማን (active trachoma) መከላከል ይቻላል?» **ዛድዋ**

«ምን ያህል መከላከያ ዘዴዎች አሉ?» **ሮቁኛ**

«ምን ምን ናቸው?» **ማስቆረጥ፣ መድሃኒትና ንጽህና**

«እንዴት እናስታውሳቸው?» «**በማመን**»

«የአይናችንን ጤና መጠበቅ ለምን አስፈለገን?»

**እይታችን ለሕይወታችን** ......

*የመምህሩ ማስታወሻ*

## ክፍለ ትምህርት ሦስት

# የትራኮማ በሽታ መተላለፊያና መከላከያ መንገዶች

**ቁልፍ መልዕክቶች:-**

«ትራኮማ እንዴት ከሰው ወደ ሰው ይተላለፋል?»

«የቆሸሹ ፊቶችና እጆች እንዲሁም የቆሸሹ ልብሶችንና ዝንቦች በሽታው ከሰው ወደ ሰው በቀላሉ እንዲተላለፍ ዋነኛውን ሚና ይጫወታሉ?»

«ያልታጠቡ ፊቶች ቆሻሻ እጆችና ልብሶች ለትራኮማ መስፋፋት ትልቁን ድርሻ ይወስዳሉ:: በተቃራኒው ዘወትር የሚታጠቡ ፊቶች ንፁህ እጆችና ልብሶች ትራኮማ እንዳይስፋፋ ያደርጋሉ::»

## የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች:-

1. ተማሪዎች የትራኮማ (active trachoma) ዋነኛው መተላለፊያ መንገዶችን ጠንቅቀው ያውቃሉ:: እንዴት በጣቶቻችን፣ መሐረቦችን በጋራ በመጠቀም፣ በዝንቦች የዓይን ጠብታዎችን በጋራ በመጠቀም፣ ወይንም በመነካካት ባክቴሪያው ከሰው ወደ ሰው ሊተላለፍ እንደሚችል ይማራሉ::
2. ተማሪዎች ስለ ትራኮማ መተላለፊያ መንገድ በተለምዶ በህብረተሰቡ የሚነገረውንና ትክክለኛውን ለይተው ይገነዘባሉ::
3. ተማሪዎች የትራኮማ (active trachoma) በሽታ የሚተላለፍባቸውንና የሚባባስባቸውን መንገዶች በመለየት ችግሩን ለመቀነስ ምን መደረግ እንዳለበት ማስረዳት ይችላሉ:: እነዚህም የማይታጠቡ ዓይኖችና እጆች የቆሸሹና የተበከሉ ልብሶችና መሐረቦች፣ ዝንቦችና የሰውም ሆነ የእንስሳት አይነ ምድር ሲሆኑ በአንፃሩ እነዚህ ሁኔታዎች በንፅህና ከተያዙ በሽታዎችን መቀነስና መከላከል እንደሚቻል ይረዳሉ::
4. ተማሪዎች፣ የተማሪ ቤተሰቦች እንዲሁም ህብረተሰቡ ትራኮማን (active trachoma) ለመከላከል ምን ማድረግ እንዳለበት በሰፊው ይማራሉ።

## ተግባራት /Activities/

1. ክለሣ: /ለ15 ደቂቃ/
2. ትራኮማ እንዴት ይመጣል? /45-60 ደቂቃ/
3. ጨዋታ የትራኮማ መተላለፊያ መንገዶች ሲጠሩ በማጨብጨብ መለየት /10 ደቂቃ/

## ክፍለ ትምህርት ሦስት

# የትራኮማ በሽታ መተላለፊያና መከላከያ መንገዶች

**ቁልፍ መልዕክቶች:-**

«ትራኮማ እንዴት ከሰው ወደ ሰው ይተላለፋል?»

«የቆሸሹ ፊቶችና እጆች እንዲሁም የቆሸሹ ልብሶችንና ዝንቦች በሽታው ከሰው ወደ ሰው በቀላሉ እንዲተላለፍ ዋነኛውን ሚና ይጫወታሉ?»

«ያልታጠቡ ፊቶች ቆሻሻ እጆችና ልብሶች ለትራኮማ መስፋፋት ትልቁን ድርሻ ይወስዳሉ። በተቃራኒው ዘወትር የሚታጠቡ ፊቶች ንፁህ እጆችና ልብሶች ትራኮማ እንዳይስፋፋ ያደርጋሉ።»

## የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች:-

1. ተማሪዎች የትራኮማ (active trachoma) ዋነኛው መተላለፊያ መንገዶችን ጠንቅቀው ያውቃሉ። እንዴት በጣቶቻችን፣ መሐረቦችን በጋራ በመጠቀም፣ በዝንቦች የዓይን ጠብታዎችን በጋራ በመጠቀም፣ ወይንም በመነካካት ባክቴሪያው ከሰው ወደ ሰው ሊተላለፍ እንደሚችል ይማራሉ።
2. ተማሪዎች ስለ ትራኮማ መተላለፊያ መንገድ በተለምዶ በህብረተሰቡ የሚነገረውንና ትክክለኛውን ለይተው ይገነዘባሉ።
3. ተማሪዎች የትራኮማ (active trachoma) በሽታ የሚተላለፍባቸውንና የሚባባስባቸውን መንገዶች በመለየት ችግሩን ለመቀነስ ምን መደረግ እንዳለበት ማስረዳት ይችላሉ። እነዚህም የማይታጠቡ ዓይኖችና እጆች የቆሸሹና የተበከሉ ልብሶችና መሐረቦች፣ ዝንቦችና የሰውም ሆነ የእንስሳት አይነ ምድር ሲሆኑ በአንፃሩ እነዚህ ሁኔታዎች በንፅህና ከተያዙ በሽታዎችን መቀነስና መከላከል እንደሚቻል ይረዳሉ።
4. ተማሪዎች፣ የተማሪ ቤተሰቦች እንዲሁም ህብረተሰቡ ትራኮማን (active trachoma) ለመከላከል ምን ማድረግ እንዳለበት በሰፊው ይማራሉ።

## ተግባራት /Activities/

1. ክለሣ: /ለ15 ደቂቃ/
2. ትራኮማ እንዴት ይመጣል? /45-60 ደቂቃ/
3. ጨዋታ የትራኮማ መተላለፊያ መንገዶች ሲጠሩ በማጨብጨብ መለየት /10 ደቂቃ/

4. ትራኮማ (active trachoma) እንዴት ይመጣል? እንዴትስ ልንከላከለው እንችላለን በሚል ርዕስ አጭር ገለፃ /ከ 45-60 ደቂቃ/

## ክፍለ ትምህርት ሦስትን ለማጠናቀቅ በግምት ወደ 2:25 ሰዓት ይፈጃል

ክለሣ: የመተላለፍያ ዋና ዋና መንገዶች
የተሰጠው ጊዜ: 15 ደቂቃ
የትምህርት መርጃ: ስለ ትራኮማ የሚተርክ መጽሐፍ
አቀራረብ: መምህሩ ከማስተማርዎ በፊት ተግባራዊ ክንዋኔዎችን ያንብቡ

1.1. መምህር ከመጽሐፉ ላይ የእያዩንና የአያቱን ታሪክ እንዲያስታውሱ ተማሪዎቹን የእያዩ አያት እንዴት የትራኮማ ጀርሞች እንደያዛቸው ይጠይቁ:: ተማሪዎቹ ይህንን በቀላሉ ማስታወስ ካልቻሉ መጽሐፉን በድጋሚ እንዲያዩት ማድረግ ወይንም እንደ አስፈላጊነቱ ታሪኩን እንደገና መተረክ /ገጽ 5 ይመልከቱ/ ተማሪዎቹ የትራኮማ በሽታ እንዴት በቆሸሹ ህፃናት ላይ በቀላሉ እንደሚተላለፍ ማስታወስ ማለትም በሚነካኩበት ወቅት ወይንም መሀረቦቻቸውን በጋራ በመጠቀም እንዲሁም በቆሻሻና በዝንቦች አማካይነት ሊያዙ እንደሚችሉ ያስታውሱ::

## *የመምህሩ ማስታወሻ*

**2. የትራኮማ በሽታ መተላለፊያ መንገዶች ሠርቶ ማሣየት**
የተሰጠው ጊዜ: ከ45-60 ደቂቃ
የትምህርት መርጃ: ተማሪዎች የሚይዙዋቸው የተለያዩ ሚና መጫወቻ ካርዶች /Role Cards/ ማዘጋጀት
አቀራረብ: መምህር ከማስተማርዎ በፊት የሚከናወኑ ድርጊቶችን /Activities/ ያንብቡ ተማሪዎች የሚለብሱዋቸው ወይንም የሚያነቧቸው የተለያዩ ጹሑፎችን ማዘጋጀት በዚህ ተግባር ተማሪዎች የተለያየ ገፀ ባህሪ ይይዛሉ:: በዚህ መሰረት

አንዳንዶቹ "የትራኮማ ጀርሞች" ከፊሎቹ ደግሞ "ዝንቦች" ሆነው ይተውናሉ:: ከዚያም እንዴት ከሰው ወደ ሰው እንደሚተላለፍ ይጫወታሉ:: መምህሩን ተማሪዎች እንዴት እንደሚተውኑ ከዚህ በታች ያለውን ያስጠኑዋቸው:: በዚህ እንቅስቃሴ የሚሳተፉ 15 ተማሪዎችን በመምረጥ ወደ ፊት ያውጡዋቸው:: መምህር የተማሪዎቹን /script/ ቃለ ተውኔት በሚገባ ማወቅ ይኖርበታል:: ይህም ተማሪዎቹን ለማበረታታትና ለማስተካከል ይጠቅማል:: የተዋናዮቹ ተማሪዎች ቁጥር ከበዛ ከክፍል ውጪ ሜዳ ላይ እንዲተውኑ ማድረግ ብዙ ተመልካቾች ትራኮማ እንዴት እንደሚሰራጭ እንዲያውቁ ያደርጋል::

2.1. ተማሪዎች በህብረተሰቡ ዘንድ ያለውን የተሳሳተ የትራኮማ በሽታ ሥርጭት ግንዛቤ ከመጨበጣቸው በተጨማሪ ዋና ዋናዎቹን የመተላለፍያ መንገዶች እንዲወያዩባቸው ያድርጉ:: ከዚያም የተነሱትን ነጥቦች በጥቁር ሰሌዳው ላይ ይፃፉ::

ለምሳሌ:- ትራኮማ እንዴት ይተላለፋል?

| ህብረተሰቡ የሚያምንባቸው የተሳሳቱ መተላለፊያ መንገዶች | |
|---|---|
| 1 | ጭስ |
| 2 | ሠይጣን |
| 3 | የአምላክ ቁጣ |
| 4 | ወዘተ |

| ትክክለኛዎቹ መተላለፊያ መንገዶች | |
|---|---|
| 1 | የቆሸሹ ጣቶች |
| 2 | ዝንቦች |
| 3 | የተበከለ ፎጣ |
| 4 | ወዘተ |

ተማሪዎች እነዚህን ዝርዝሮች ከመምህራቸው ብዙ እርዳታ ሳይሹ ቢዘረዝሩዋቸው ይመረጣል:: መምህር ስለ ትራኮማ ታሪክ ይንገሯቸው:: በዚህን ጊዜ ተማሪዎች በዝርዝራቸው ውስጥ አዳዲስ ነጥቦች እንዲጨምሩ ይረዳቸዋልና:: ከዚህ በታች ያለው ምንባብ የተማሪዎችን አመለካከት እንደሚያጠናክር ይታመናል::

2.2. መምህር ተማሪዎች መፃፍ ትተው በጥሞና እንዲያዳምጡ በማድረግ ይህን ምንባብ ያንብቡላቸው::

የትራኮማ ጀርም በሰዎች ውስጥ መኖር የሚችል ጉጂ ጀርም ነው:: ይህ ጀርም የሰዎችን ዓይን በመቆርቆርና በማሳበጥ የሚያሳምም በመጨረሻም ለዓይነ ስውርነት የሚዳርግ ነው:: ጀርሙ በትራኮማ ሕመም ከተጠቁ ሰዎች ዓይንና አፍንጫ በሚወጣ ፈሳሽ ቆሻሻ ውስጥ ይኖራል:: ሆኖም ጀርሙ በአንድ ቦታ ተወስኖ መኖር አይችልም:: ስለዚህ በሰዎችና በዝንቦች አማካይነት ከቦታ ወደ ቦታ ከበሽተኛ ወደ ጤነኛ በመዘዋወር ይዛመታል::

አንዳንዴ ይህ የጀርሞች ዝውውር በእጅ ጣቶች አማካይነት ይከናወናል:: በትራኮማ ከተያዛችሁና ዓይናችሁን ከነካካችሁ የትራኮማ ጀርሙ ቀጥሎ ወደምትነኩበት ቦታ በቀላሉ ይጓዛል: ሌሎችን ስትነኩ ወይንም ስትጨብጡ እነርሱን ይበክላል:: እነርሱንም ሆነ እናንተን በሽተኛ ያደርጋል::

<u>ማልቀስ</u>:- ትራኮማን ያመጣል? በፍፁም አያመጣም ዕንባ ይህን ጀርም አይፈጥርም:: ሆኖም አልቅሳችሁ ዓይናችሁን ስትጠርጉ ጀርሙን ወደ ዓይናችሁ እንዳታደርሱ ተጠንቀቁ ምክንያቱም ጀርሙ እጃችሁን እንደ መጓጓዣ ይጠቀማልና::

አልፎ አልፎ የትራኮማ ጀርም ለመተላለፊያነት የቆሸሹ ልብሶችን ወይም መሃረቦችን ይጠቀማል:: ይህ የሚሆነው ፊቱን በበሽታው የተጠቃ ሰው በመሃረብ ተናፍጦ ወይንም ፊቱን ጠርጎበት ለሌላ ጓደኛው መሃረቡን እንዲጠቀም ሲያደርግ ነው:: በተጨማሪም እናቶች የልጆቻቸውን ፊት ለማበስ የቆሸሹ ጨርቆችን ሲጠቀሙ ጀርሙ ይህን አጋጣሚ በመጠቀም ይጓዛል::

የትራኮማ ጀርም <u>ጭስን</u> እንደመጓጓዣ ይጠቀማል? ጭስ የትራኮማን ጀርም ከአንድ ቦታ ወደ ሌላው ቦታ አያጓጉዝም :: በእርግጥ ጭስ በተፈጥሮ የአይንን ምቾት ይነሣል (ያጨናብሳል) ሆኖም ግን የትራኮማን ጀርም ከቦታ ወደ ቦታ አያጓጉዝም::

ከዚህ በተጨማሪ ከቆሻሻ ቦታ የሚነሱ ዝንቦች ከሁሉም በበለጠ የትራኮማ ጀርምን ያሰራጫሉ:: ዝንቦችና የትራኮማ ጀርሞች በጣም የጠነከረ ወዳጅነት አላቸው:: አንድ ዝንብ ከበሽተኛ ሰው ዓይን ላይ ካረፈ በኋላ ጤነኛው ሰው ዓይን በሚያርፍበት ወቅት ጀርሙ በቀላሉ ይተላለፋል:: በዚህ መልክ በዙ ሰዎች ለበሽታው ይጋለጣሉ::

<u>አፈር/አቧራ/ብናኝ</u> የትራኮማ በሽታን ያስተላለፋሉ? ይህ በፍፁም እውነት አይደለም:: ዝንቦች የቆሸሹ ህፃናትን ይመርጣሉ እንጂ አቧራ ብቻውን በራሱ ትራኮማ አያስተላልፍም::

በአጠቃላይ የህመምተኛን ዓይን የሚነካና የጤነኛውን ዓይን ሊነካ የሚችል ነገር የትራኮማን ጀርም በቀላሉ ያስተላልፋል:: ይህ የመከላከያ መድሃኒቱን ማስቀመጫ ብልቃጡንም (የቴትራሳይክሊን መድሐኒት ቲዩብ)ን ይጨምራል:: የቴትራሳይክሊን መድሐኒትን ስትጠቀሙ ጀርሙ በቀላሉ ወደ ዓይን ለመግባት ጊዜ አይወስድበትም::

<u>እግዚአብሔር</u> ትራኮማን ያስተላልፋል? ይህ ትልቅ ስህተት ነው:: እግዚአብሔርም

ሆነ ሰይጣን የትራኮማን ጀርም አያስተላልፉም:: ይህ ከእውነት የራቀና በተለምዶ የሚነገር ግምት ብቻ ነው::

የትራኮማ በሽታ በዘር የሚተላለፍ አይደለም:: ከቤተሰባችሁ አንድ ወይንም ሁለት ሰዎች በትራኮማ ተይዘው ነበር ማለት እናንተ መያዛችሁ አይቀርም ማለት አይደለም:: ዋናው የበሽታውን መምጫ መንገዶች አውቆ አስፈላጊውን ጥንቃቄ በማድረግ መከላከል ነው::

2.3. መምህር ታሪኩን አንብበው ሲጨርሱ ተማሪዎች ድራማ እንደሚሰሩ ይንገሩዋቸው:: ከዚያም 15 ተማሪዎችን ለዚህ ተግባር ይምረጡ:: እያንዳንዱ ተማሪ የተለያዩ ፖስተሮችን (ካርዶችን) ከነጽሑፋቸው ይለብሳሉ ወይንም የተፃፈባቸውን ካርዶች ይይዛሉ::

ከጽሑፎቹ መካከል «የትራኮማ ጀርም» «የእጅ ጣቶች» «የቆሸሸ ልብስ» «ዝንብ» «የመድሐኒት ብልቃጥ/ቲዩብ» «ጭስ» « አዋራና አፈር» «እንባ» «እግዚአብሔር» «ሠይጣን» እንዲሁም «በዘር» የሚሉ ናቸው:: ከነዚህ በተጨማሪ «ሰዎች» የሚሉ ሰባት ጽሑፎችን ይዘጋጃሉ:: ሁሉም ካርዶች ለተመልካች በግልጽ የሚታዩ ሆነው መቅረብ አለባቸው::

2.4 መምህር ለመተወን ፈቃደኛ የሆኑትን ተማሪዎች የሰሙትን ታሪክ እንዴት እንደሚጫወቱ አስተያየታቸውን ይጠይቁ:: መምህር ቢያንስ አንድ ጊዜ ዝግጅቱን በደንብ ማየት ይኖርባቸዋል። ትዕዛዙንም ታሪኩንም በድጋሚ ሳያነቡ ይስጡዋቸው:: መተወን ከመጀመራቸው በፊት የተመረጡትን ስድስቱን ሰዎች ወደ ተማሪዎቹ ፊታቸውን አዙረው እንዲቆሙ፣ ከዚያም «የትራኮማ ጀርም» የሚለውን ፖስተር የያዘውን ተማሪ አንድ ተማሪ ፊት በጣም ተጠግቶ እንዲቆም ማድረግ::

2.4.1 «ጣቶች ትራኮማን ያስተላልፋሉን?» መምህር ይጠይቃሉ መልስ አዎ! የሚል መሆን አለበት:: «የእጅ ጣቶች» የሚል የተፃፈበትን ጽሑፍ የያዘ ተማሪ ወደ «ትራኮማ ጀርም» እንዲጠጋ ይታዘዛል:: ከዚያም እጆቹን/ዋን ይዞ ወደ አንድ «ሰው» እንዲያደርሰው በማድረግ ይበክለዋል:: ከዚያም ሁለቱም («የእጅ ጣቶች»ና «የትራኮማ ጀርም») ወደ ሁለተኛው «ሰው» ይሄዱና እንዲሁ ይበክላሉ:: ተማሪዎች በሚገባ እንቅስቃሴያቸውን እስኪረዱ መምህር አስፈላጊውን ድጋፍ ያድርጉላቸው::

2.4.2. «ተማሪዎች! እንባ ትራኮማን ያስተላልፋልን» መምህር ይጠይቃሉ ተማሪዎች አያስተላልፍም ብለው መመለስ አለባቸው:: ከዚያም «እንባ» ወደ «ትራኮማ ጀርም» በመሄድ ወደ ሦስተኛ ሰው ለመውሰድ እንዲሞክር ማድረግ በዚህ ወቅት «የትራኮማ ጀርሙ» ባለመንቀሳቀስ በእንባ ትራኮማ ጀርም እንደማይተላለፍ በግልፅ ያሳያል:: ከዚያም ይህ እንደማይሆን ባሉበት በመቆየት ተማሪዎች ይጫወቱታል::

2.4.3. «ተማሪዎች! የቆሻሻ ልብስ ወይንም መሃረብ ትራኮማን ያስተላልፋሉን?» መምህር ይጠይቃሉ መልሱ 'አዎን ያስተላልፋሉ' መሆን አለበት:: ከዚያም «ቆሻሻ ልብስ/መሐረብ» በሚል ፅሑፍ የያዘው ተማሪ «የትራኮማን ጀርም» ወደ አራተኛው ሰው ይዞ እንዲሄድ መጠየቅ::

2.4.4. መምህር ከላይ የተጠቀሱትን መሰል ጥያቄዎች በተለያዩ መንገዶች የተለመደውንም ሆነ ትክክለኛውን ይጠይቁ:: ተማሪዎች እንዴት እንደሚንቀሳቀሱ ከተረዱ በኋላ መምህር የተውኔቱን ፅሑፍ (script) በዝግታ ያንብቡላቸው ተማሪዎችም እንደሰሙት ገፀ-ባህሪውን ይጫወቱ:: የትራኮማን ጀርም ሆኖ የሚሠራው በጣም መጥፎ ገፀ ባህሪን ተላብሶ ቢተውን ለታሪኩ ተአማኒነትና ውበትን ይሰጠዋል:: ዝንቦችን ሆነው የሚሠሩትም እንዲሁ ቢያደርጉ ይመረጣል:: እንደሰው ሆነው የሚተውኑት «የትራኮማ ጀርሙ» ሲነካቸው እንደበሽተኛ ሆነው ይተውናሉ:: ይህ ትዕይንት ተማሪዎቹን ባዝናና መጠን ታሪኩን ለሌሎች በበለጠ እንዲያስረዱ ይጋብዛቸዋል::

2.5. መምህር ተማሪዎቹ ትዕይንቱን በደንብ እስኪያጠኑትና ከእርስዎ ምንም እርዳታ ሳይሹ በሚገባ መተወን እስኪችሉ ድረስ ቃለ ተውኔቱን (script) በመደጋገም ያስጠኑዋቸው::

**አስተውሎት**:- ተማሪዎች ትዕይንቱን በጣም ከወደዱት ተዋናይ ተማሪዎችን በመቀያየር እንዲጫወቱትና እንዲከልሱት ማድረግ ይቻላል:: ፅሑፉን ለብዙ ጊዜ በመስማታቸውም ከመምህሩ ምንም ዕርዳታ ሳያገኙ የራሳቸውንም በመጨመር እንዲተውኑት ማድረግ ይቻላል::

በተመሣሣይ ሁኔታ መምህሩም ሆኑ ተማሪዎች ከትምህርት ቤታቸው ውጪ ይህንን ትዕይንት ለማቅረብ የተቻላቸውን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል:: አጎራባች ተማሪዎችም በህብረት በመቀናጀት ወደ የመኖሪያ ሥፍራቸው በመሄድ እንዲያቀርቡ ማመቻቸት:: ይህንን ለማድረግ መፈክሮች (ፅሑፎች) የግድ ወሳኝ አይደሉም:: በምትኩ ተማሪዎች እራሳቸውን በማስተዋወቅ ለምሣሌ «እኔ የትራኮማ ጀርም ነኝ» ፣ «እኔ ዝንብ

ነኝ» ወዘተ በማለት ተግባራቸውን መግለፅ ወይም የሚጫወቱትን ገፀ ባህሪ ማስተዋወቅ ይችላሉ::

2.6. መምህር ከዚህ በፊት ያስጀመሩዋቸውን የሚከተለውን ሠንጠረዥ ተማሪዎች በሚገባ ስለመረዳታቸው ለማወቅ በቡድን ወይም አጠገባቸው ከተቀመጠው ጋር በመሆን እንዲወያዩና እንዲጨርሱ ያበረታቱዋቸው:: በመጨረሻም ተማሪዎቹ ይህንን የመሰለ የተሟላ ሠንጠረዥ እንዳሉዋቸው ያረጋግጡ::

| ህብረተሰቡ የሚያምንባቸው የተሳሳቱ መተላለፊያዎች |
|---|
| 1. ጭስ |
| 2. ሠይጣን |
| 3. ማልቀስ |
| 4. አዋራ/አፈር |
| 5. በዘር |
| 6. እግዚአብሔር |

| ትክክለኛ የመተላለፊያ መንገዶች |
|---|
| 1. የቆሸሹ ጣቶች |
| 2. የቆሸሹ መሀረቦች |
| 3. ዝንቦች |
| 4. የዓይን መድሃኒት መያዣ ዎችና የጠብታ ብልቃጦች በጋራ መጠቀም |

ከሠንጠረገፑ ቀጥሎ ተማሪዎች የራሳቸውን ዋና ዋና ቁልፍ ነጥቦች እንዲፅፉ መጠየቅ::

«ትራኮማ እንዴት ከሰው ወደ ሰው ይተላለፋል?» የቆሸሹ እጆችና ጨርቆች፣ በጋራ የምንጠቀምባቸው የዓይን መድሃኒት መያዣዎች፣ የጠብታ ብልቃጦችና ከቆሻሻ ላይ የሚነሱ ዝንቦች ትራኮማን በቀላሉ ከሰው ወደ ሰው እንዲተላለፍ ያደርጋሉ።

## የመምህሩ ማስታወሻ

## 3. ጨዋታ፡ ትራኮማ በሽታን የሚያስተላልፉ መንገዶችን በጭብጨባ መጠቆም

**የተሰጠው ጊዜ፡ ወደ 10 ደቂቃ**

**የትምህርት መርጃ፡ ምንም አያስፈልግም**

**አቀራረብ፡ ከማስተማርዎ በፊት የሚደረጉ ድርጊቶችን /Activities/ ማንበብ**

3.1. ይህ ጨዋታ ግሩምና የሚያነቃቃ ሆኖ ተማሪዎቹ እንዲንጫጩ ያደርጋል:: መምህሩ ከዚህ በፊት የተማሩትን ሁለቱንም ሁኔታዎች (ትክክለኛውንና የተሳሳተውን መተላለፊያ መንገድ) በድንገት ይጠራል/ ትጠራለች:: (የራሳቸውንም የተሳሳተ መተላለፍያ መንገዶች መጨመር ይቻላል):: ተማሪዎቹ በጥሞና እያዳመጡ ትክክለኛ መተላለፊያ መንገድ በመምህሩ በተጠራ ቁጥር ሁለት ጊዜ ያጨበጭባሉ:: ከተሳሳቱ ግን ማጨብጨባቸውን ትተው ፀጥታ በማስፈን ያሳልፋሉ:: ይህ ጨዋታ የተማሪዎችን ጠንቅቆ የማዳመጥና የመለየት ችሎታ ስለሚጠይቅ ይኸው ይገለፅላቸው:: ጨዋታውን ማፋጠን ፈታኝነቱንም ከመጨመሩ ባሻገር ለጨዋታው ውበትን ይሰጣል:: ስለዚህ መምህር ይህን ዘዴ እንደ አስፈላጊነቱ መጠቀም ይችላሉ::

**ለምሳሌ፡** «የእጅ ጣቶች»

ሁለት ጊዜ ማጨብጨብ /ቸብቸብ/

«የእጅ መሀረቦች»

ሁለት ጊዜ ማጨብጨብ /ቸብቸብ/

«የእጅ ጣቶች»

ሁለት ጊዜ ማጨብጨብ /ቸብቸብ/

«ጭስ»

ሁለም ፀጥ! ያጨበጨበ አለ እንዴ?

3.2. በመጨረሻም መምህር ከተማሪዎች መካከል በመምረጥ ጨዋታውን እንዲያጫውቱ ዕድል ይስጡዋቸው::

## የመምህሩ ማስታወሻ

**4. የትራኮማን ተላላፊነት የሚያባብሱ ወይም የሚቀንሱ ሁኔታዎችን ለይቶ ማቅረብ**
**የተሰጠው ጊዜ፡** 45-60 ደቂቃ
**የትምህርት መርጃ፡** ቆሻሻ አካባቢን የሚያመለክት ሥዕልና የትራኮማን አስከፊነት ደረጃ በደረጃ የሚያሳይ ስዕል
**አቀራረብ፡ ከማስተማርዎ በፊት የሚደረጉ ድርጊቶችን /Activities/ ማንበብ**

4.1. ከላይ የተመለከትነው እንቅስቃሴ ሙሉ ተግባር (activity) ዋና ዓላማው የትራኮማን መተላለፊያ መንገዶች አውቀን እንዴት በሽታውን መከላከል እንደምንችል በሚገባ ለማጤን የሚያስችል ነው፡፡

መምህር ለተማሪዎች እንዲህ ይበሉዋቸው «የትራኮማ ጀርም እንዴት ከሰው ወደሰው እንደሚተላለፍ አይተናል፡፡ ይህም በቀጥታ በጣቶቻችን አማካኝነት፣ በተዘዋዋሪ ደግሞ በቆሸሹ ልብሶችና የቆሸሹ መሐረቦችን በጋራ በመጠቀምና በዝንቦች ወዘተ ነው፡፡ ይህንን በሚገባ በምናይበት ወቅት እንዴት ልንከላከለው እንደምንችል ምን ተገነዘብን? ይህ ማለት መነካካትና እቃ በጋራ መጠቀም ላይኖርብን ነውን? ይህንንስ ማድረግ እንችላለን? የእያዩና የአያቱን ታሪክ ታስታውሳላችሁ? የእያዩ አያት ትራኮማን ስለመከላከል ምን ነበር ያሉት? ተማሪዎች ንፅህና እንደሚያስፈልግ ማስታወስ ይኖርባቸዋል ይህም ፊታችንና እጃችንን ዘወትር መታጠብና አካባቢያችንንም በንፅህና መጠበቅን ያካትታል፡፡ መምህር ቁልፍ መልዕክቶችን በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ተማሪዎች በደብተራቸው እንዲፅፉ ያድርጉ፡፡

«የቆሸሹ ፊቶችና እጆች እንዲሁም ልብሶች እንዴት የትራኮማ ጀርም ከሰው ወደ ሰው ለመተላለፍ ሁኔታዎችን እንደሚያመቻቹ በአንፃሩ ደግሞ ንፁህ ፊቶች፣ እጆችና ልብሶች በተጨማሪም ንፅህናው የተጠበቀ አካባቢ በሽታው እንዳይተላለፍ እንደሚረዳ» ይፃፉላቸው፡፡

4.2. መምህር የቆሻሻ አካባቢን የሚያሳይ ፖስተር ለተማሪዎች ያሳዩ በምሥሉም የሚታዩትን ችግሮች ተማሪዎቹ ማብራራት አለባቸው፡፡ በመጀመሪያ ተማሪዎቹ በህብረት ስለሚያዩአቸው ችግሮችና ከትራኮማ ጋር ስላላቸው ግንኙነት ይወያዩበታል፡፡ እንዲሁም ከቁልፍ መልዕክቶች (በክፍለ ትምህርት ሦስት ከተጠቀሱት) ጋር በማነፃፀር በሚገባ ይረዱታል፡፡ ይህንኑ በደብተራቸው ይፃፉ፡፡ መምህር እባክዎ ከአምስት ደቂቃዎች በሁዋላ የተማሪዎችን አስተያየት ይሰብስቡ፡፡ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን «ችግሮች» ለበለጠ መረጃ ይመልከቱ፡፡

4.3. ተማሪዎች ከሥዕሉ ላይ ያስተዋሉዋቸውን የትራኮማን ተላላፊነት የሚያባብሱ «ችግሮችን» ዝርዝር ከፃፉ በኋላ መምህር ይህን በመሰለ አካባቢ ማን መኖር

እንደሚፈልግ ይጠይቁ፡፡ በመቀጠልም ይህን የመሰለ ቆሻሻ አካባቢ መኖር ወይም የአካባቢን ንፅህና አለመጠበቅ ለትራኮማ በሽታ እንደሚያጋልጥ አስረግጠው ይንገሩዋቸው፡፡ ይህን ችግር ለመፍታት ምን መደረግ አለበት በሚል ርዕስ ተማሪዎች አጠገባቸው ከሚገኘው ሰው ጋር እንዲነጋገሩበት ከ5-10 ደቂቃ ይስጡዋቸው፡፡ ከዚያም አንድ ምሳሌ በህብረት ከተማሪዎች ጋር መሥራት፡፡

**ለምሣሌ፡-** «በቤት አካባቢ የሚፀዳዳ ህፃን» በዚህ ጊዜ ተማሪዎች ከመጽሐፉ ውስጥ የእያዩ አያት እያዩን ትንሽ እህቱን ወደ መፀዳጃ ቤት እንዲወስዳት ወይንም አየነምድሯን እንድትቀብር እንዲያደርግ የመከሩትን ማስታወስ አለባቸው፡፡ በመቀጠልም ህፃናት ከተጸዳዱ በኋላ ዓይነምድራቸው ላይ አፈር መጨመር (መመለስን) እንዲያውቁት ማድረግ፡፡ ይህም ደግሞ ዝንቦች በቀላሉ እንዳያገኙት ያደርጋቸዋል፡፡ ተማሪዎች ይህን እንዴት ማድረግ እንዳለባቸው መጠየቅ፡፡ ይህን ለማድረግ እንጨት ወይንም ትንሽ መቆፈሪያ መጠቀም አለባቸውን? እነዚህን ዕቃዎች ለመፀዳዳት በወጡ ቁጥር ይዘው መሄድ ሊኖርባቸው ነውን? ከዚያም ከዘረዘሩዋቸው ችግሮች አጠገብ የራሳቸውን መፍትሄ የሚሉዋቸውን ሀሳቦች እንዲፅፉ ማድረግ፡፡ ተማሪዎቹ ተገቢውን የመፍትሄ ሀሳቦች መስጠታቸውን ማረጋገጥና በክፍለ ጊዜው መጠናቀቂያ ተማሪዎቹ የችግሮቹንና የመፍትሄዎችን ዝርዝር በትክክል በደብተራቸው ላይ እንዲጽፉ ማድረግ፡፡

| ያሉ ችግሮች | መፍትሄዎች |
|---|---|
| - በቤት አካባቢ የሚፀዳዳ ህፃን | - ህፃናት በየቦታው ከመፀዳዳት ይልቅ ሽንት ቤትን እንዲጠቀሙ ማድረግ/አይነምድራቸውን እንዲቀብሩ ማድረግ |
| - ዝንቦች በበዙበት ሥፍራ የሚጫወት ፊቱና እጆቹ የቆሸሸ ህፃን | - ህፃናት በቆሸሹ ቁጥር ፊታቸውንና እጃቸውን መታጠብ፣ ቢያንስ በቀን ሁለት ጊዜ ትልልቅ ልጆች ታናናሾቻቸውን እንዲታጠቡ መርዳት/ማጠብ |
| - በቤት አቅራቢያ የሚገኝ የተቆለለ ቆሻሻና ንፅህናው ያልተጠበቀ መጸዳጃ ቤት | - አካባቢን በንፅህና መያዝ ዝንቦችን ማስወገድ፣ ዓይነምድርን ከቤት አርቆ ማስወገድ ወይንም መቅበር<br>- መፀዳጃ ቤትን ማፅዳት |
| - ውሃ ማጠራቀሚያዎች በውሃ እጥረት ባዶ ሲሆኑ ፊትንም ሆነ እጅን ለመታጠብ አለመቻል | - ፊትንም ሆነ እጅን ለመታጠብ በቂ የሆነ ውሃን ሁልጊዜ ማዘጋጀት፡፡ |
| - የሰውና እንስሳት ዓይነምድር | - የሰውንም ሆነ የእንስሳትን ዓይነ-ምድር ቆፍሮ አርቆ ማስወገድና በየቦታው አለመበተን |
| - በምሥሉ ላይ የሚታዩ ልብሳቸው በጣም የቆሸሹ ሰዎች | -ዘወትር ልብስን ማጠብ<br>- የግል ንፅህናን መጠበቅ |

4.4. እዚህ ነጥብ ላይ ሲደርሱ መምህር ለተማሪዎች «የትራኮማን እድገት ደረጃ የሚያሳየውን ፖስተር» በዝርዝር መከለስ ይኖርባቸዋል:: በትረካ መጽሐፍ የተጠቀሰውን የትምህርቱ ዓላማ የሆነውን ንፅህናን በማስረገጥ ማስረዳትም አስፈላጊ ነው:: «ንፅሕና» የትራኮማ በሽታ ሥርጭት ዋነኛው ጠላት ነው::

4.5. መምህር ወረቀትና እርሳስ (ቢገኝ ከለሮች) ለተማሪዎች በመስጠት የትራኮማ በሽታ መከላከያ የሆነውን የንፅህናን እንቅስቃሴ የሚያሣይ ሥዕል እንዲስሉ ማድረግ (ከነዚህም ሰዎች ፊታቸውን ሲታጠቡ፣ እጃቸውን ሲታጠቡ፣ ልብስ ሲያጥቡ፣ ቤት ሲያፀዱ፣ ሽንት ቤት ሲጠቀሙ ወዘተ):: ሥዕሎቹ በሙሉ ለክፍሉ ለእይታ ይቀርባሉ:: መምህሩም ሰዎች በሥዕሉ ላይ የታዩትን እንቅስቃሴዎች በሙሉ ቢፈፅሙ ትራኮማን መከላከል እንደሚችሉ በመደጋገም ያስረዱዋቸው:: «(ማመን)»

በተጨማሪም ከተቻለ «የቆሻሻ አካባቢ»ን ተቃራኒ እንቅስቃሴ የሚያሳይ «የንፁህ አካባቢ» ምሥልን ተማሪዎች ሠርተው እንዲያሳዩ መገፋፋት ሥዕሉን ሲጨርሱ ህብረተሰቡ ከላይ የተመለከተውን እንቅስቃሴ ካደረገና የአካባቢውን ንፅህና ከጠበቀ ጤና ሊሆን እንደሚችል ሁለቱን አካባቢዎች በማነፃፀር አበክረው ያስረዷቸው::

# የትራኮማ ቀንን ስለማቀድ

በትራኮማ ቀን አከባበር ላይ የሚቀርቡ ፕሮግራሞችን በቅድሚያ መምረጥ በመምህሩ መምሪያ ዋና ዓላማ መሠረት መምህራን በመደበኛ የአካባቢ ሣይንስ ትምህርት ክፍለ ጊዜያቸው ስለትራኮማና ስለመከላከያና መቆጣጠሪያ ዘዴዎቹ አካትተው በማስተማራቸው የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች ከመደበኛ ተማሪዎቹ በተጨማሪ ስለበሽታው ግንዛቤን የሚያስጨብጥ ፕሮግራም እንዲሆን ይደረጋል። በዚሁ ዕለት በድራማ መልክ ለሚቀርበው ዝግጅት የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎችን ማመቻቸት። ይኸውም፣

- ተግባራዊ ክንዋኔዎችን የሚከውኑ ከተማሪዎች የተውጣጡ ቡድኖችን መምረጥ
- የድራማውን ታሪክ በጥንቃቄ መምረጥ
- በድራማው ውስጥ ያለው የጤና ትምህርት መልዕክት «ትራኮማን መከላከል»ን በግልጽ እንዲያሳይ ማድረግ
- ገጸ ባሕሪያትን በጥንቃቄ በመምረጥ በቂ ዝግጅት እንዲያደርጉ ማገዝ
- ለድራማው የሚያስፈልጉ አልባሳትና ሌሎች መገልገያዎችን በቅድሚያ ማዘጋጀት፣

ለዕለቱ አከባበር በአቅራቢያው ኃላፊነት የተሰጣቸው ግለሰቦች፣ የጤና ባለሙያዎች እንዲሁም የትራኮማ በጎ ፈቃደኞች ስለዕለቱ በቅድሚያ በማሳወቅ ዝግጅቱ መቼ፣ የት እና እንዴት መቅረብ እንዳለበት ሀሳብ እንዲሰጡ በመጋበዝ ከነዚሁ የሕብረተሰብ ክፍሎች ጋር የተቀናጀ ዝግጅት የሚቀርብበትን ሁኔታ ማመቻቸት።

**ተቀፅላ 1**

***መገምገሚያ ቅጽ***

ይህ ቅጽ የተዘጋጀው የሥርዓተ ትምህርቱ መምሪያ ውጤታማነት ምን ደረጃ እንደደረሰ ለመገንዘብ ነውና እባክዎን በየክፍለ ትምህርቱ መጨረሻ ለነዚህ ጥያቄዎች መልስ ይስጡባቸውና ለርዕሰ መምህሩ ወይም ለሚመለከተው ክፍል ያስረክቡዋቸው:: መልሶቻችሁና አስተያየታችሁ ሥርዓተ ትምህርትን የበለጠ ለማሻሻል ትልቅ ሚና ይኖረዋል:: በተለይ የእርስዎ የባለሙያው/ዋ ሀሳብ ለትምህርቱ ሥራ ትልቅ ግብዓት (input) ለመማር ማስተማሩ ውጤት (out put) ወሳኝ ነውና::

የክፍለ ትምህርቱ ቁጥር ______________

1. በትምህርቱ የተሳተፉ ተማሪዎች ብዛት ______________
2. የዕድሜ ክልላቸውና የክፍል ደረጃቸው ______________
3. ለዚህ ክፍለ ትምህርት የሚያገለገሉ የጤና ትምህርት መርጃዎች______________
4. ክፍለ ትምህርቱ የወሰደው ጊዜ ( በሰዓት የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን ጨምሮ) ______________
5. የተከናወኑ እንቅስቃሴዎች ብዛት ______________
6. የተዘጋጁ እንቅስቃሴዎች (activities) ለተማሪዎች በእርግጥ ይመጥኑ ነበር? ወይንስ የግልዎን ማሻሻያ መጠቀም ነበረብዎት?
7. ተማሪዎቹን በጣም ያስደሰታቸውና በትክክል የተገበሩት እንቅስቃሴ (activity) የትኛው ነበር?
8. ለመተግበር የከበዳችሁ እንቅስቃሴ የቱ/የትኞቹ ነበሩ? ለምን?
9. የዘለሉዋቸው እንቅስቃሴዎች /ድርጊቶች የትኞቹ ናቸው? ለምን?
10. ይህን ክፍለ ትምህርት በድጋሚ ማስተማር ቢኖርብዎት በየትኛው ላይ ማሻሻል የሚያደርጉ ይመስሎታል?


**ለትብብርዎ እናመሰግናለን::**

# TRACHOMA GRADING CARD

- Each eye must be examined and assessed separately.
- Use binocular loupes (x 2.5) and adequate lighting (either daylight or a torch).
- Signs must be clearly seen in order to be considered present.

The eyelids and cornea are observed first for inturned eyelashes and any corneal opacity. The upper eyelid is then turned over (everted) to examine the Conjunctiva over the stiffer part of the upper lid (tarsal conjunctiva).

The normal conjunctiva is pink, smooth, thin and transparent. Over the whole area of the tarsal conjunctiva there are normally large deep-lying blood vessels that run vertically.



*Normal tarsal conjunctiva (x2 magnification). The dotted line shows the area to be examined.*

***TRACHOMATOUS INFLAMMATION - FOLLICULAR (TF)***: the presence of five or more follicles in the upper tarsal conjunctiva.

Follicles are round swellings that are paler than the surrounding conjunctiva, appearing white, grey or yellow, Follicles must be at least 0.5mm in diameter, i.e., at least as large as the dots shown below, to be considered.





*Trachomatous inflammation - follicular (TF).*

***TRACHOMATOUS INFLAMMATION - INTENSE (TI):*** *pronounced inflammatory thickening of the tarsal conjunctiva that obscures more than half of the normal deep tarsal vessels.*

The tarsal conjunctiva appears red, rough and thickened. There are usually numerous follicles, which may be partially or totally covered by the thickened conjunctiva.



*Trachomatous inflammation - follicular and intense (TF + TI).*

***TRACHOMATOUS SCARRING (TS):*** *the presence of scarring in the tarsal conjunctiva.*


Scars are easily visible as white lines, bands, or sheets in the tarsal conjunctiva. They are glistening and fibrous in appearance. Scarring, especially diffuse fibrosis, may obscure the tarsal blood vessels.



*Trachomatous scarring (TS)*

***TRACHOMATOUS TRICHIASIS (TT):*** *at least one eyelash rubs on the eyeball.*


Evidence of recent removal of inturned eyelashes should also be graded as trichiasis.



*Trachomatous trichiasis (TT)*

***CORNEAL OPACITY (CO):*** *easily visible corneal opacity over the pupil.*

The pupil margin is blurred viewed through the opacity. Such corneal opacities cause significant visual impairment (less than 6/18 or 0.3 vision), and therefore visual acuity should be measured if possible.



*Corneal opacity (CO)*

**TF:– give topical treatment (e.g. tetracycline 1%).**

**TI:– give topical and consider systemic treatment.**

**TT:– refer for eyelid surgery.**

**WORLD HEALTH ORGANIZATION**
**PREVENTION OF BLINDNESS AND DEAFNESS**

**Support from the partners of the WHO Alliance for the Global Elimination of Trachoma is acknowledged.**

LIONS - CARTER CENTER
SightFirst Initiative

የአማራ ክልላዊ መንግስት
ጤና ጥበቃ ቢሮ
Amhara Regional Health
Bureau

# ማመን (SAFE)

## ትራኮማን ለመቆጣጠር ዓይነተኛ ሥልት!

**S**urgical Correction



**ማ**
የዓይን ቆብን በቀዶ ሕክምና
ማስተካከል (ማስቆረጥ)

**A**ntibiotic Application




**መ**
የዓይን መድሐኒት ሳያቋርጡ
መጠቀም

**F**acial Cleanliness



**ን**
የፊትን ንፅሕና መጠበቅ
(ፊትን አዘውትሮ መታጠብ)

**E**nvironmental Sanitation



**ን**
የአካባቢን ንፅሕር መጠበቅ

**ስለ ትራኮማ ሲያወሱ ማመንን አይርሱ!**
**ማየት ማመን ነው!**

The Carter Center
ካርተር ሴንተር

# ትራኮማ ቀስ በቀስ ለዓይነ ስውርነት ይዳርጋል

የአማራ ክልላዊ መንግስት
ጤና ጥበቃ ቢሮ
Amhara Regional Health Bureau




## በትራኮማ ምክንያት የሚመጣ ዓይነ ስውርነትን መከላከል ይቻላል

Lion Clubs International